# ጠቅላላ ይዘት


፩. ግእዝ

፪. ሰዋስወ ግእዝ

፫. ግስ

፬. አብዛኅያን

፭. አገባባት

፮. ገቢር ተገብሮ

፯. ዘርፈ ሰዋስው

፰. ሥርዓተ ንባብ


## ማሳሰቢያ

- ትምህርቱ ግእዝ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች በቃላቸው እንዲያጠኑት ማድረግ ያስፈልጋል።
- በየምዕራፎቹ መጨረሻ ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሠሩ ማድረግ ይገባል።
- ትምህርቱ በሚሠጥበት ወቅት ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት ያስፈልጋል።
- በተሰጡ ምሳሌዎች መሠረት ተማሪዎች በክፍል ውስጥም በግብረ ቤትም ተጨማሪ ምሳሌዎችን እንዲያቀርቡ ተግባራትን መስጠት ያስፈልጋል

# <u>መክሥት</u>


<u>ርዕስ</u> <u>ገጽ</u>

ሙባዕ ........................................ IV

ምዕራፍ አንድ

፩.ግእዝ ........................................ ፩

፩.፩. ትርጓሜ ........................................ ፩

፩.፪. የግእዝ ታሪክ ........................................ ፩

፩.፫. ፊደል ........................................ ፩

፩.፫.፩. ትርጓሜ ፊደል ........................................ ፩-፫

፩.፫.፪. ተረክቦ ፊደል ........................................ ፬

ምዕራፍ ኹለት

፪. ስዋሰወ ግእዝ ........................................ ፭

፪.፩. መራሕያን ........................................ ፭-፯

፪.፪. አመልካቾች ........................................ ፯-፰

፪.፫. አገናዛቢዎች ........................................ ፰-፲

ቃለ ተዋስዖ ........................................ ፲፩

ምዕራፍ ሦስት

፫. ግስ ........................................ ፲፪

፫.፩. ትርጓሜ ግስ ........................................ ፲፪

፫.፪. አርዕስተ ግስ ........................................ ፲፪

፫.፫. ረብሐ ግስ ........................................ ፲፪-፲፫

፫.፬. የግስ አዋጅ ........................................ ፲፫-፲፬

፫.፭. ረብሐ ግስ ዘሰመንቱ ........................................ ፲፭-፳፪

፫.፮. አሥራው ፈደላት ........................................ ፳፫

፫.፯. አዕማድ ........................................ ፳፫-፳፬

፫.፯. የአኃዝ ርባታ ........................................ ፳፬-፳፮

ምዕራፍ አራት

፬. አብዛኀያን ........................................ ፳፯

፬.፩. አብዛኀያን ፊደላት ........................................ ፳፯

፬.፪. የራብዕ ብዛት ........................................ ፳፯

፬.፫. የካዕብ ብዛት ........................................ ፳፯

፬.፬. የብዙ ብዙ ........................................ ፳፯

፬.፭. ምልስ ብዛት ........................................ ፳፰

፬.፮. የሥም ብዛት ........................................ ፳፰

፬.፯. የሣልስ ቅጽል ብዛት ........................................ ፳፰

፬.፰. የሳድስ ቅጽል ብዛት ........................................ ፳፱

፬.፱. የባዕድ ቅጽል ብዛት ........................................ ፳፱

፬.፲. የማይበዙ ሥሞች ........................................ ፳፱

፬.፲፩. ነጠላም ብዙም ሥሞች ........................................ ፳፱

ምዕራፍ አምስት

፭. አገባባት ........................................ ፴

፭.፩. ዐቢይ አገባብ ........................................ ፴

፭.፪. ደቂቅ አገባብ ........................................ ፴-፴፩

፭.፫. ንዕስ አገባብ ........................................ ፴፩

ምዕራፍ ስድስት

፮. ገቢር ተገብሮ ........................................ ፴፪

**መባዕ፡-** ዝንቱ ጽሕፈት ተደለወ ለወጣንያን አርድዕት ከመ ያእምሩ ጣዕመ ልሳነ ግእዝ ከመ ይምራኆዎ ኀበ ዐቢይ ወብዙኅ አእምሮተ ምሥጢራተ ቅኔ ወመጻሕፍት። በእንተ ኮነ አልቦ ጉልቁ ምሥጢሩ ለልሳነ ግእዝ። እስመ ውእቱ ልሳን ሰማያዊ ዘተወሀበ ለመላእክት እምነ እግዚአብሔር ወሶበ ተፈጥሩ። ወእንለእመሕያውኒ ተወክፈ እምነ መላእክት ከመ ይሰብሆ ለአምላኩ ምስሌሆሙ። ወሀገሪትነ ኢትዮጵያ ይእቲ አቃቢተ ልሳነ ግእዝ እም ጥንት እስከ ናሁ ወቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ዘኢትዮጵያ በነኪር ኵነት ገብረት ኵሎ መዛግብቲሃ በአእምሮ ሊቃውንቲሃ። በከመ ይቤ መጽሐፍ "ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ" ንሕነ ንግበር ከመ ንኩን ደቂቀ አበዊነ ሊቃውንት በተምህሮ ለባሕረ ጥበባት ልሳነ ግእዝ ለጠይቆተ ምሥጢራተ መጻሕፍት። ዝንቱ ጽሑፍ አስተሐደለ ምዕራፍ ሰመንቱ እሉኒ ፩. በእንተ ግእዝ ፪. ሰዋስወ ግእዝ ፫. ግስ ፬. አብዛኅያን ፭. አገባባት ፮. ገቢር ተገብሮ ፯. ዘርፈ ሰዋስው ፰. ሥርዓተ ንባብ እሙንቱ። ዝ ውእቱ አእምሮ ሕያው ዘረከብናዎ እም አፈ ሊቃውንት ዘይውኅዝ በቃንዮተ ድሕንጻ መንፈስ ቅዱስ። የጊ ድልዋኒነ ንንበር ከመ ንስተይ እም ዝንቱ ማየ አእምሮ።

# ልሳነ ግእዝ

## ምዕራፍ አንድ

## ፩. ግእዝ

### ፩.፩. ትርጓሜ

ግእዝ *"አግአዘ"* ካለው ግስ የተገኘ ሲሆን ፍቺም **ነፃ አወጣ** ማለት ነው፡፡ ምስክሩም *"ፈቀደ እግዚእ **ያግእዞ** ለአዳም ኅዙነ ወትኩዘ ልብ ልቡ ያዘነና የተከዘ አዳምን **ነፃ ያወጣው** ዘንድ ወደደ፡፡"* እንዲል ሊቁ አባ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም ዘሰኑይ፡፡

***አንድም*** **ግእዝ** *ማለት ፣ አንደኛ ፣ የመጀመሪያ ፣ ቀዳሚ ማለት ነው ቋንቋው ጥንታዊ ቀዳማዊ የመላእክት እና የአዳም ቋንቋ ነውና፡፡*

*አንድም* **ግእዝ** *ማለት ጉንድ ዋሕድ እንደማለት ነው ጉንድነቱም አጽቅ ተብሎ በተቋመ ወርቅ ይመስላልና፡፡*

### ፩.፪. የግእዝ ታሪክ

*በአጭሩ ጠቅለል ተደርጎ ሲገለጽ የሀገር ውስጥም የውጭ ሊቃውንትም ግእዝ ሴማዊ ነው ካማዊ ነው እያሉ ቢከራከሩም ቋንቋው በብሔር የተሰየመ አለመሆኑን ስሙ ይገልጥልና እንደ እብራይስጥ እንደ ፅርዕ እንደ እንግሊዘኛ እንደ ፈረንሳይኛ በሀገራችን እንዳሉት እንደ ኦሮምኛ እንድ አማርኛ እንደ ትግሬኛ በተናጋሪዎች ተሰይሞ አይነገርም ስሙ ግእዝ ነው ማለት ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ግን በጣም የሚያስማማው ሀሳብ ግእዝ **የመላእክትና** **የአዳም** ቋንቋ መሆኑ ነው ለዚህ ደግሞ ማስረጃ የሚሆነን ለአባታችን ለኢትዮጵያዊው ለቅዱስ ያሬድ የተገለፀለት የዝማሬ ስልትና ቋንቋ ነው፡፡*

*የግእዝ ቋንቋ መካነ ልደቱም፣ መካነ ዕድገቱም ኢትዮጵያ እንደመሆኑ መጠን ያበረከተው አስተዋጽኦ እጅግ ጥልቅና ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይም ለማኅበራዊ፣ ለፖለቲካዊና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገቶች መሠረት የጣለ ሲሆን በተለይ በማኅበራዊ ዘርፍ ኪነ ጥበባዊ ዕድገት ላይ ያበረከተውን አስተዋጽዖ በተመለከተ ጥቂቶቹን ለመጠቅስ ያህል ከላይ የጠቀስነው ያሬዳዊ ዜማ፣ ሥርዓተ ጽሕፈትና ሥነ ጽሑፍ፣ ፍልስፍና ኪነ ህንጻና የዘመን አቆጣጠር ቀመር (ባሕረ ሐሳብ) ወ.ዘ.ተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡*

### ፩.፫. ፊደል

### ፩.፫.፩. ትርጓሜ ፊደል

*ፊደል በብዙ ሁኔታ ይተረጎማል ከነዚህም አንደኛው "ፊደል" የሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺ ነው፡፡ ሁለተኛውም "የፊደል ምሥጢራዊ ቁጥር" ትርጉም ነው፡፡ ሦስተኛውም የእያንዳንዱ ነገረ ሃይማታዊ ትርጉም ነው፡፡ ሁለቱን ማለትም "ፊደልንና የፊደልን ምሥጢራዊ ትርጉም" ከዚህ የማስቀምጥ ሲሆን "የፊደልን ነገረ ሃይማኖታዊ ትርጉም" ግን ተማሪዎች (አንባቢያን) በራሳቸው ልዩ ልዩ የግእዝ መጻሕፍትን በማንበብና በመመርመር እንዲተረጉሙ እጠቁማለሁ*

**"ፊደል"** *'ፈደለ' ጣፈ፣ ቆጠረ፣ ለየ፣ መረጠ ካለው ግስ የተገኘ ሲሆን ፊደል ማለትም ጥፈት፣ ቁጥር፣ ልዩ፣ ምርጥ ማለት ነው፡፡* **አንድም** *ፊደል ማለት መሠረተ ቃል ወሰዋስው፣ መሠረተ አንቀጽ ወመጻሕፍት፣ ፍኖተ ምስጢራት ወጥበባት እና ፈለገ ልሳናት የቋንቋና የቃል የአነጋገር ኹሉ ምልክት አምሳል መግለጫ ወይም ማስታወቂያ ማለት ነው፡፡ ፊደል ባይኖር ኖሮ እነዚህ ሁሉ አይኖሩም ነበርና፡፡*

*የግእዝ ፊደላት እስከ አባ ሰላማ ግእዝ ብቻ የነበሩ ሲሆን ከአባ ሰላማ ዘመን ጀምሮ በመደብ ፳፮ እያንዳንዳቸው ፯ ፯ ቅንጣት ያላቸው ሆነዋል ይህም በግእዝ ላይ ስድስቱ አዕጹቅ ካዕብ፣ ሣልስ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስና ሳበዕ ተጨምሮባቸዋል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ፊደላት እያንዳንዳቸው የራሳቸው* **ቁጥራዊ ትርጉም** *አላቸው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

**ፊደላቱና ቁጥራቸው፦**

| ተ.ቁ | ፩ | | ፪ | | ፫ | | ፬ | | ፭ | | ፮ | | ፯ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ሀ | ፩ | ሁ | ፪ | ሂ | ፫ | ሃ | ፬ | ሄ | ፭ | ህ | ፮ | ሆ | ፯ | ፩ |
| ፪ | ለ | ፪ | ሉ | ፬ | ሊ | ፮ | ላ | ፰ | ሌ | ፲ | ል | ፲፪ | ሎ | ፲፬ | ፪ |
| ፫ | ሐ | ፫ | ሑ | ፮ | ሒ | ፱ | ሓ | ፲፪ | ሔ | ፲፭ | ሕ | ፲፰ | ሖ | ፳፩ | ፫ |
| ፬ | መ | ፬ | ሙ | ፰ | ሚ | ፲፪ | ማ | ፲፮ | ሜ | ፳ | ም | ፳፬ | ሞ | ፳፰ | ፬ |
| ፭ | ሠ | ፭ | ሡ | ፲ | ሢ | ፲፭ | ሣ | ፳ | ሤ | ፳፭ | ሥ | ፴ | ሦ | ፴፭ | ፭ |
| ፮ | ረ | ፮ | ሩ | ፲፪ | ሪ | ፲፰ | ራ | ፳፬ | ሬ | ፴ | ር | ፴፮ | ሮ | ፵፪ | ፮ |
| ፯ | ሰ | ፯ | ሱ | ፲፬ | ሲ | ፳፩ | ሳ | ፳፰ | ሴ | ፴፭ | ስ | ፵፪ | ሶ | ፵፱ | ፯ |
| ፰ | ቀ | ፰ | ቁ | ፲፮ | ቂ | ፳፬ | ቃ | ፴፪ | ቄ | ፵ | ቅ | ፵፰ | ቆ | ፶፮ | ፰ |
| ፱ | በ | ፱ | ቡ | ፲፰ | ቢ | ፳፯ | ባ | ፴፮ | ቤ | ፵፭ | ብ | ፶፬ | ቦ | ፷፫ | ፱ |
| ፲ | ተ | ፲ | ቱ | ፳ | ቲ | ፴ | ታ | ፵ | ቴ | ፶ | ት | ፷ | ቶ | ፸ | ፲ |
| ፲፩ | ኀ | ፳ | ኁ | ፵ | ኂ | ፷ | ኃ | ፹ | ኄ | ፻ | ኅ | ፻፳ | ኆ | ፻፵ | ፳ |
| ፲፪ | ነ | ፴ | ኑ | ፷ | ኒ | ፺ | ና | ፻፳ | ኔ | ፻፶ | ን | ፻፹ | ኖ | ፪፻፲ | ፴ |
| ፲፫ | አ | ፵ | ኡ | ፹ | ኢ | ፻፳ | ኣ | ፻፷ | ኤ | ፪፻ | እ | ፪፻፵ | ኦ | ፪፻፹ | ፵ |
| ፲፬ | ከ | ፶ | ኩ | ፻ | ኪ | ፻፶ | ካ | ፪፻ | ኬ | ፪፻፶ | ክ | ፫፻ | ኮ | ፫፻፶ | ፶ |
| ፲፭ | ወ | ፷ | ዉ | ፻፳ | ዊ | ፻፹ | ዋ | ፪፻፵ | ዌ | ፫፻ | ው | ፫፻፷ | ዎ | ፬፻፳ | ፷ |
| ፲፮ | ዐ | ፸ | ዑ | ፻፵ | ዒ | ፪፻፲ | ዓ | ፪፻፹ | ዔ | ፫፻፶ | ዕ | ፬፻፳ | ዖ | ፬፻፺ | ፯ |
| ፲፯ | ዘ | ፹ | ዙ | ፻፷ | ዚ | ፪፻፵ | ዛ | ፫፻፳ | ዜ | ፬፻ | ዝ | ፬፻፹ | ዞ | ፭፻፷ | ፹ |
| ፲፰ | የ | ፺ | ዩ | ፻፹ | ዪ | ፪፻፸ | ያ | ፫፻፷ | ዬ | ፬፻፶ | ይ | ፭፻፵ | ዮ | ፮፻፴ | ፺ |
| ፲፱ | ደ | ፻ | ዱ | ፪፻ | ዲ | ፫፻ | ዳ | ፬፻ | ዴ | ፭፻ | ድ | ፮፻ | ዶ | ፯፻ | ፻ |
| ፳ | ገ | ፪፻ | ጉ | ፬፻ | ጊ | ፮፻ | ጋ | ፰፻ | ጌ | ፻፻ | ግ | ፻፻፪፻ | ጎ | ፻፻፬፻ | ፪፻ |
| ፳፩ | ጠ | ፫፻ | ጡ | ፮፻ | ጢ | ፱፻ | ጣ | ፻፻፪፻ | ጤ | ፻፻፭፻ | ጥ | ፻፻፰፻ | ጦ | ፪፻፻፻ | ፫፻ |
| ፳፪ | ጰ | ፬፻ | ጱ | ፰፻ | ጲ | ፻፻፪፻ | ጳ | ፻፻፮፻ | ጴ | ፪፻፻ | ጵ | ፪፻፻፬፻ | ጶ | ፪፻፻፰፻ | ፬፻ |
| ፳፫ | ጸ | ፭፻ | ጹ | ፻፻ | ጺ | ፻፻፭፻ | ጻ | ፪፻፻ | ጼ | ፪፻፻፭፻ | ጽ | ፫፻፻ | ጾ | ፫፻፻፭፻ | ፭፻ |
| ፳፬ | ፀ | ፮፻ | ፁ | ፻፻፪፻ | ፂ | ፻፻፰፻ | ፃ | ፪፻፻፬፻ | ፄ | ፫፻፻ | ፅ | ፫፻፻፮፻ | ፆ | ፬፻፻፪፻ | ፮፻ |
| ፳፭ | ፈ | ፯፻ | ፉ | ፻፻፬፻ | ፊ | ፪፻፻፩፻ | ፋ | ፪፻፻፰፻ | ፌ | ፫፻፻፭፻ | ፍ | ፬፻፻፪፻ | ፎ | ፬፻፻፱፻ | ፯፻ |
| ፳፮ | ፐ | ፰፻ | ፑ | ፻፻፮፻ | ፒ | ፪፻፻፬፻ | ፓ | ፫፻፻፪፻ | ፔ | ፬፻፻ | ፕ | ፬፻፻፰፻ | ፖ | ፭፻፻፮፻ | ፰፻ |

የፊደልን ምሥጢር በተመለከተ የተወሰኑ ምሳሌውች እንደሚከተለው ቀርበዋል፦

***ምሳሌ ፩፦*** የግእዝ ፊደላት ብዛት ከግእዝ እስከ ሳብዕ ያሉት በአጠቃላይ ብዛታቸው ፳፮*፯ = ፻፹፪ ናቸው ይህ ቁጥር በእስራኤል የቀን አቆጣጠር የ፫ ወራት ወይም የ፩ ሩብ ዓመት የቀናት ብዛት ነው። ይህስ እንዴት ነው ቢሉ *"በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ"* ተብሎ በዘፍጥረት ፩፥፩ ላይ እንደተመዘገበው እግዚአብሔር ፍጥረትን መፍጠር የጀመረው በዕለተ እሁድ ሚያዚያ አንድ ቀን ነው እስራኤል ይህንን ቀንና ወር መነሻ በማድረግ ቀን ይቆጥሩ ነበር ይህም በሚከተለው ሰንጠርዥ ተገልጿል።

| ቁጥር | ሩቤዎች | መነሻ | | መድረሻ | | የቀን ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወሩ | ዕለቱ | ወሩ | ዕለቱ | |
| ፩ | ፩ኛ ሩብ ዓመት | ሚያዚያ | እሁድ | ሚያዚያ | ሰኞ | ፴ |
| ፪ | | ግንቦት | ማክሰኞ | ግንቦት | ረቡዕ | ፴ |
| ፫ | | ሰኔ | ሐሙስ | ሰኔ | ቅዳሜ | ፴፩ |
| ፬ | ፪ኛ ሩብ ዓመት | ሐምሌ | እሁድ | ሐምሌ | ሰኞ | ፴ |
| ፭ | | ነሐሴ | ማክሰኞ | ነሐሴ | ረቡዕ | ፴ |
| ፮ | | መስከረም | ሐሙስ | መስከረም | ቅዳሜ | ፴፩ |
| ፯ | ፫ኛ ሩብ ዓመት | ጥቅምት | እሁድ | ጥቅምት | ሰኞ | ፴ |
| ፰ | | ህዳር | ማክሰኞ | ህዳር | ረቡዕ | ፴ |
| ፱ | | ታህሣስ | ሐሙስ | ታህሣስ | ቅዳሜ | ፴፩ |
| ፲ | ፬ኛ ሩብ ዓመት | ጥር | እሁድ | ጥር | ሰኞ | ፴ |
| ፲፩ | | የካቲት | ማክሰኞ | የካቲት | ረቡዕ | ፴ |
| ፲፪ | | መጋቢት | ሐሙስ | መጋቢት | ቅዳሜ | ፴፩ |
| **ጠቅላላ የዓመቱ የቀን ብዛት** | | | | | | ፫፻፷፬ |

ከላይ በሰንጠርዡ በተገለጸው መሰረት የሁለት ሩብ ዓመቶች ወይም የግማሽ ዓመት የቀናት ብዛት (፴+፴+፴፩)*፪ = ፻፹፪ ነው ይህ ደግሞ የፀሐይን ፲፪ መሳክው ተከትሎ ሲቆጠር ፮ቱ መሳክው በምሥራቅ ፮ቱ መሳክው ደግሞ በምዕራብ ስለሚገኙ ፀሐይ ደግሞ ወጥታ ስለማትቀር ጠልቃም ስለማትቀር ታጥፎ ስለሚቆጠር (፻፹፪*፪ = ፫፻፷፬) እንጂ ምሥጢሩስ ከግእዝ ፊደል ጋር እንዲህ የተገናኘ ነው። ከዚህ የተነሳ የግእዝ ፊደል ትርጉሙ ረቂቅ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

**ምሳሌ ፪**. አርዮስ ***"ወልድ ፍጡር ውእቱ"*** ብሎ ሲክድ ምስክር ይሆነኛል ብሎ የጠቀሰው በመጽሐፈ ጥበብ ፩፥፬ ላይ ***"ቀዳሜ ኩሉ ተፈጥረተ ጥበብ"*** የሚለውን ነበር መንፈስ ቅዱስ ባወቀ ፫፻፲፰ቱ ሊቃንት ተሰብስበው እንዲያወግዙት አደረገ ይህም ጠ : ፫፻፣ በ : ፱፣ በ : ፱ ⟹ ፫፻ + ፱ + ፱ = ፫፻፲፰ አርዮስ በካደበት ቃል ተወግዞበታል።

**ምሳሌ ፫**. ***"ወአዘዞ እግዚአብሔር ለአዳም"*** በሚለው የመጽሐፍ አነጋገር ውስጥ የአዳምን የሥሙን ትርጓሜ ስናይ

አ:፵፣ ደ:፻፣ መ:፬ ⟹ ፵+፻+፬ = ፻፵፬ **"ኤዶም"** የሚለውም የፊደሉ ቁጥር እንደዚሁ ፻፵፬ መሆኑ ለአዳም የተሰጠችው መኖሪያ ቦታ ለእሱ የተመቸች የተስማማች መሆኗን የሚያሳይ ነው። ይህን ባለማወቃቸው ግን አንዳንዶቹ **"ኤደን"** ብለው በመጻፍ ምሥጢር ሲያፋልሱ ይስተዋላል።

**ምሳሌ ፬**. ዘፍጥ ፲፯፥፭ ***"ወኢይሰመይ እንከ ስምከ አብራም አላ ትሰመይ አብርሃም"*** ብሎ በስሙ አንድ ፊደል ጨመረለት ይህም አስቀድሞ ይጠራበት የነበረው ስሙ ***አብራም*** አ:፵ በ:፱ ረ:፮ መ:፬ ፵+፱+፮+፬=፶፱ ለ፷ አንድ ስለጎደለው ምሥጢር ያሟላ ዘንድ ቁጥሩ ፩ የሆነውን *'ሀ'*ን ጨመረለትና አበ ብዙኃን መሆኑን አረጋገጠለት። ይህ እንዴት ነው ቢሉ ፷ ቁጥር ዋና መሰረት ሆኖ ፭ት ፲፪ቶችን ያስገኛል ከ፷ ቁጥር ፭ት አስራ ሁለቶች እንደተገኙ ከአብርሃምም ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል ተገኝተዋል ምሥጢሩ እንዲህ ይገናኛል። እዚሁ ላይ ***"ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ሣራ ብእሲትከ ኢትሰመይ እንከ ሣራ አላ ይኩን ስማ ሳራ"*** አለው እንደዚህ ማለቱ የፊደል ስሟ በግእዙ ፊደል *'ሠ'* ፭ ቁጥር የነበረው ቀርቶ *'ሰ'* የሆነበት ምክንያት የስሟን ትርጉም በምሥጢር ከእናቷ ከሄዋን ጋር ለማገናኘት ነው። ይህ እንዴት ነው ቢሉ ሄዋን ሲል ሀ:፩፣ ወ:፷፣ ነ:፴ ፩+፷+፴ = ፺፩ ይህ ቁጥር ለ፯ ሲካፈል ፲፫ ይሆናል ሳራ ሲል ሰ:፯፣ ረ:፮ ፯+፮ = ፲፫ ስለሆነ የሄዋንና የሳራ ሥም እንዲህ እንዲገናኝ ያደረገው የፊደል ምሥጢር ነው።

**ምሳሌ ፭**· ማር ፫፥፲፮ ***"ወሰመዮ ለስምዖን ጴጥሮስ"*** ፈታሒ ናዛዚ መሆኑን በምሥጢር የሚገልፀው ***ስምዖን*** የሚለው ሳይሆን ***ጴጥሮስ*** የሚለው መሆኑን ሲያጠይቅ ነው። ይህ እንዴት ነው ቢሉ ***"ዘአሠርክዎ በምድር ይከውን እሡረ በሰማያት ወዘፈታሕክዎ በምድር ይከውን ፍቱሐ በሰማያት"*** ከሚለው አንቀጽ ውስጥ **ፍቱሐ** የሚለውን ቃል ወስደን የምሥጢሩን መገናኘት እንይ **ጴጥሮስ** ሲል ጰ:፬፻፣ ጠ:፫፻፣ ረ:፮፣ ሰ:፯ ፬፻+፫፻+፮+፯ = ፯፻፲፫ **ፍቱሐ** ሲል ፈ:፯፻፣ ተ:፲፣ ሐ:፫ ፯፻+፲+፫ = ፯፻፲፫ የፊደል ምሥጢር ረቂቅና ሰፊ በመሆኑ ጥቂት ማሳያ ለማቅረብ እንጂ ተምህርቱን በዚህ መጨረስ የሚቻል ሆኖ አይደለም። *(ምንጭ፦ አስረስ የኔሰው ዘብሔረ ጎጃም "የካም መታሰቢያ" ከሚለው መጽሐፋቸው)*

ከላይ ባየነው ዝርዝር ሐሳብ መሠረት ፊደላት የየራሳቸው ምሥጢራዊ ትርጉም ስላላቸው ተመኩሳይያን ፊደላት ላይ ያለው "በዝተዋልና ይቀነሱ" የሚለው ዘመቻ የፊደልን አጠቃቀም ካለማወቅ ወይም የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም ለማበላሸት የሚደረግ ነው። ተመኩሳይያት ፊደላት የሚባሉት ሀ፡ ሐ፡ ኀ፣ ሠ፡ ሰ፣ አ:ዐ እና ጸ፡ ፀ ሲሆኑ የኔታ ዐቢይ ለቤዛ ዐምደ ግእዝ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ ፲፬ ላይ *"ተመኩመሳይያን ፊደላት ማለት ሞክሼዎች ተመሳሳዮች ማለት ሲሆን እነዚህ ፊደላት ተመኩሳይያን የተባሉበት ዋና ምክንያት በድምጽ አንድ ስለሆኑ ነው። ነገር ግን ምንም እንኳ በድምጽ አንድ ቢሆኑም ቅሉ በምሥጢር በትርጉምና በቅርጽ ግንኙነት የላቸውም"* በማለት ገልጸዋቸዋል። ይህ ማለት ሃሌታው "ሀ" ሐመሩ "ሐ"ን ወይም ብዙኃኑ "ኀ"ን፣ ንጉሡ "ሠ" እሳቱ "ሰ"ን፣ አልፋው "አ" ዐይኑ "ዐ"ን እና ጸሎቱ "ጸ" ፀሐዩ "ፀ"ን የማይተካ የማይወክል መሆኑን በመረዳት ፊደላችን ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ጎልታ ከምትታወቅባቸው የዘመን አቆጣጠርና የአሥራ ሦስት ወር ፀጋ ቀጥሎ የሚታወቅ ሀብት በመሆኑ ከአጽራረ ፊደላት ጥቃት መጠበቅ ያስፈልጋል።

## ፩.፫.፪. ተረክቦ ፊደል

ፊደልን ማን አገኘው ቢሉ የአዳም ሣልሳይ ትውልድ የሆነው <u>ሄኖስ</u> እንዳገኘው ተገልጿል፡፡ ሄኖስ ማለት ነባቢ፣ ለባዊ ህያው ማለት ነውና ስሙ ከግብሩ የተስማማ የደብር ቅዱስ ሰው ከፈጣሪው ተሹሞና ቀሶ የሚያዝ የሚናዝዝ የታቦተ ሕጉ ዐቃቢና ገበዝ የመሲሑ ጸሐፌ ትዕዛዝ ስለኾነ አውታረ ልቡናው በድሕንጻ መንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶለት ፊደሉን ከቋንቋው ቋንቋውን ከፊደል አስማምቶ ቀኝ እጁን በነፍስ ግራ እጁን በሥጋ ዐሥር ጣቶቹን በዐሥርቱ ቃላት መስሎ አነጻጽሮ በአንደበቱና በጣቱ እያነበበና እየጣፈ የፊደልን ሥራ ከሕግና ከትእዛዝ ጋራ አምልቶ አስፍቶ አስተምሯል ፊደልም በዚህ ጊዜ እንደታወቀ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ከዚህ በኋላም ጥቅመ ሰናዖር ሲፈርስ ቋንቋ ሲከፋፈል ሁሉም የራሱን ቋንቋ ይዞ በየአቅጣጫው ሲበተን ፊደልም በየቋንቋው በየነገዱ በተናጋሪዎች እያደገ እየሰፋ መጥቶ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደረሷል ማለት ነው፡፡ ግእዝ ግን ሳይከፋፈል ተጠብቆ እስከዚህ ደርሷል ጥንታዊ የአዳምና የመላእክት ቋንቋ ያሰኘው ቅሉ ይህ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ፪· ሰዋስወ ግእዝ

### ፪·፩· መራሕያን

መራሕያን የተባሉ አሥር ናቸው እነሱም፦

| ቁጥር | ግእዝ | አማርኛ | ቁጥር | ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | አነ | እኔ | ፮ | አንትን | እናንተ (አንስት) |
| ፪ | ንሕነ | እኛ | ፯ | ውእቱ | እሱ |
| ፫ | አንተ | በቁሙ | ፰ | ይእቲ | እሷ |
| ፬ | አንቲ | አንቺ | ፱ | ውእቶሙ | እነሱ |
| ፭ | አንትሙ | እናንተ | ፲ | ውእቶን | እነሱ (አንስት) |

አሥሩ መራሕያን ከአንዳንድ ግሶች ጋር፦

***ምሳሌ፦*** ግሶች ሰበከ፣ አጥመቀ፣ ነደገ፣ ኰነ እነዚህ ግሶች በቅርብ ርባታ ጊዜ የመጨረሻ ፊደላቸውን እያጠበቁ የሚኼዱ በመሆናቸው የተለየ ፀባይ ያሳያሉ። ሲረቡም፦

ሰበከ

| መራሕያን | ግስ | አማርኛ |
|---|---|---|
| አነ | ሰበኩ | እኔ አስተማርኩ |
| ንሕነ | ሰበክነ | እኛ አስተማርን |
| አንተ | ሰበከ | አንተ አስተማርክ |
| አንቲ | ሰበኪ | አንቺ አስተማርሽ |
| አንትሙ | ሰበክሙ | እናንተ አስተማራችሁ |
| አንትን | ሰበክን | እናንተ አስተማራችሁ |
| ውእቱ | ሰበከ | እሱ አስተማረ |
| ይእቲ | ሰበከት | እሷ አስተማረች |
| ውእቶሙ | ሰበኩ | እነሱ አስተማሩ |
| ውእቶን | ሰበካ | እነሱ አስተማሩ |

አጥመቀ

| መራሕያን | ግስ | አማርኛ |
|---|---|---|
| አነ | አጥመቁ | እኔ አጠመኩ |
| ንሕነ | አጥመቅነ | እኛ አጠመቅን |
| አንተ | አጥመቀ | አንተ አጠመክ |
| አንቲ | አጥመቂ | አንቺ አጠመቅሽ |
| አንትሙ | አጥመቅሙ | እናንተ አጠመቃችሁ |
| አንትን | አጥመቅን | እናንተ አጠመቃችሁ |
| ውእቱ | አጥመቀ | እሱ አጠመቀ |
| ይእቲ | አጥመቀት | እሷ አጠመቀች |
| ውእቶሙ | አጥመቁ | እነሱ አጠመቁ |
| ውእቶን | አጥመቃ | እነሱ አጠመቁ |

ኀደገ

| መራሕያን | ግስ | አማርኛ |
|---|---|---|
| አነ | ኀደ<u>ጉ</u> | እኔ ተውኩ |
| ንሕነ | ኀደግነ | እኛ ተውን |
| አንተ | ኀደ<u>ገ</u> | አንተ ተውክ |
| አንቲ | ኀደ<u>ጊ</u> | አንቺ ተውሽ |
| አንትሙ | ኀደ<u>ግ</u>ሙ | እናንተ ተዋችሁ |
| አንትን | ኀደ<u>ግ</u>ን | እናንተ ተዋችሁ |
| ውእቱ | ኀደገ | እሱ ተወ |
| ይእቲ | ኀደገት | እሷ ተወች |
| ውእቶሙ | ኀደጉ | እነሱ ተዉ |
| ውእቶን | ኀደጋ | እነሱ ተዉ |

ኰነ

| መራሕያን | ግስ | አማርኛ |
|---|---|---|
| አነ | ኰንኩ | እኔ ተውኩ |
| ንሕነ | ኰ<u>ነ</u> | እኛ ተውን |
| አንተ | ኰንከ | አንተ ተውክ |
| አንቲ | ኰንኪ | አንቺ ተውሽ |
| አንትሙ | ኰንክሙ | እናንተ ተዋችሁ |
| አንትን | ኰንክን | እናንተ ተዋችሁ |
| ውእቱ | ኰነ | እሱ ተወ |
| ይእቲ | ኰነት | እሷ ተወች |
| ውእቶሙ | ኰኑ | እነሱ ተዉ |
| ውእቶን | ኰና | እነሱ ተዉ |

***ማስታወሻ፡-*** ከላይ ያየናቸው ግሶች በአሥሩ መራሕያን በሚረቡበት ጊዜ በ*'ቀ'*፣ በ*'ከ'*፣ በ*'ገ'* የሚያልቁ ግሶች ***አነና ውእቶሙ፣ አንተና ውእቱ*** እንዲሁም በ*'ነ'* የሚያልቁ ግሶች ሲረቡ ደግሞ ***ንሕነና ውእቱ*** በቅርጽ ስለሚመሳሰሉ ተማሪዎች የመራሕያኑን ልዩነት ካላወቁ የንባብ ችግር ስለሚያጋጥማቸው በጥንቃቄ መረዳት ያስፈልጋል።

**መራሕያን ሦስት ዓይነት አገልግሎት አላቸው። እነሱም፦**

**ሀ· ምድብ ተውላጠ ሥም፦**

| መደብ | ነጠላ | ብዙ | ፆታ |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ | አነ | ንሕነ | የወል |
| ፪ኛ | አንተ | አንትሙ | ተባዕት |
| | አንቲ | አንትን | አንስት |
| ፫ኛ | ውእቱ | ውእቶሙ | ተባዕት |
| | ይእቲ | ውእቶን | አንስት |

ምድብ ተውላጠ ሥም ማለት ሥምን ተክቶ በሥም ቦታ እየገባ የሚያገለግል ማለት ነው። ወይም በአጭሩ ማሰሪያ አንቀጽ ማለት ይሆናል።

**ምሳሌ፦ ፩· <u>ሶምሶን</u>** ቀተለ አንበሳ።

<u>**ውእቱ**</u> ቀተለ አንበሳ። ***ውእቱ*** በሶምሶን ቦታ የገባ ምድብ ተውላጠ ሥም ነው።

<u>**ቀተለ**</u> አንበሳ። ***ቀተለ*** ያለው በውስጡ <u>**ውእቱን**</u> ይዞ ይገኛል።

፪· **ኤልያስ**! ለምንት መጻዕከ ኀበ ዝየ?

**አንተ!** ለምንት መጻዕከ ኀበ ዝየ?

ለምንት ***መጻዕከ*** ኀበ ዝየ? ***መጻዕከ*** ያለው በውስጡ **ውእቱን** ይዞ ይገኛል::

***ለ· መራሕያን እንደ ነባር አናቅጽ ሲያገለግሉ፦*** በዚህ ጊዜ እነዚህ መራሕያን እንደ መደበኛ ግሶች ማሰሪያ ሆነው ያገለግላሉ:: ከአሥሩ **ውእቱ** ተለይቶ ለቅርብና ለሩቅ፣ ለነጠላ ለብዙ፣ ለሴትና ለወንድ ሲያገለግል ሌሎቹ በየሥፍራቸው ይነገርባቸዋል ከዚህ የተነሳ **ውእቱ** ለዋጭ ተለዋጭ ፀባይ ያለው ነው:: ማለትም "**ውእቱ**" ነኝ ፥ነበርኩ ፥ እኖራለሁ ፥ ልኑር፣ ነን ፥ ነበርን ፥ እንኖራለን ፥ እንኑር፣ ነህ ፥ ነበርክ ፥ ትኖራለህ ፥ ኑር፣ ነሽ ፥ ነበርሽ ፥ ትኖሪያለሽ ፥ ኑሪ፣ ናችሁ ፥ ነበራችሁ ፥ ትኖራላችሁ ፥ ኑሩ፣ ነው ፥ ነበር ፥ ይኖራል ፥ ይኑር፣ ናት ፥ ነበረች ፥ ትኖራለች ፥ ትኑር፣ ናቸው ፥ ነበሩ ፥ ይኖራሉ ፥ ይኑሩ፣ ተብሎ በአሥሩም መራሕያን ይፈታል::

**ምሳሌ፦** አንተ **ውእቱ** አምላክ አማልክት ወእግዚአ አጋእዝት::

አምላክ **አንተ** ለኩሉ ዘሥጋ ወለኩላ ዘነፍስ::

**አነ** እትኀከ አቢይ ዘአፈቅርከ::

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ላይ የተሰመረባቸው ግእዛውያት ቃላት ውእቱ፣ አንተ እና አነ በተለመደ ማንነታቸው መራሕያን ሆነው ሳይሆን ነባር አናቅጽ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ ምክንያቱም ሌላ መደበኛ ግስ ወይም ማሰሪያ አንቀጽ ሳያስፈልግ ራሳቸው ዐረፍተ ነገሮችን አስረዋቸዋልና::

***ሐ· መራሕያን እንደ አመልካች ቅጽል፦*** መራሕያን እንደ አመልካች ቅጽል በሚያገለግሉበት ጊዜ አንድ ነገር ከተናጋሪው ያለውን የቦታ ርቀትና ቅርበት ይጠቁማሉ ማለት ነው::

| | | |
|---|---|---|
| ውእቱ | ዝስኩ | ያ |
| ይእቲ | እንትኩ | ያቺ |
| ውእቶሙ | እልኩ | እነዚያ (ተባዕታይ) |
| ውእቶን | እልኮን | እነዚያ (አንስታይ) |

**ምሳሌ፦** **ውእቶሙ** አበው ነገሩነ በእንተ ልደተ ክርስቶስ::

**ውእቶን** አንስት ሖራ ውስተ ደብረ ጽዮን::

**ይእቲ** ኢየሩሳሌም ሀገረ ሠላም ይእቲ::

**ውእቱ** መስፍን ዐቀባ እምነ ጸላዒ ለዛቲ ኢየሩሳሌም::

የተሰመረባቸው ግእዛውያት ቃላት **ውእቶሙ** ፣ **ውእቶን** ፣ **ይእቲ** እና **ውእቱ** እንደ አመልካች ቅጽል መሆናቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል::

## ፪·፪· አመልካቾች (Demonstratives)

አመልካቾች ማለት በዐረፍተ ነገር ውስጥ እየገቡ የአንድን ነገር ርቀትና ቅርበት (ቦታን) ሴትና ወንድ (ፆታን) እና ነጠላና ብዙ (ቁጥርን) የሚያመለክቱ ግእዛውያት ቃላት ናቸው:: እነዚህን አመልካቾች በዋናነት ከቦታ አንጻር በሁለት ክፍል ከፍለን እናያቸዋለን::

፩· የቅርብ አመልካቾች

| ነጠላ | ብዙ | ፆታ | መደብ |
|---|---|---|---|
| ዝንቱ/ዝ | እሎ/እሉ/እሎንቱ | ተባዕት | ፫ኛ |
| ዛቲ/ዛ | እሎን/እላ/እላንቱ | አንስት | |

፪· የሩቅ አመልካቾች

| ነጠላ | ብዙ | ፆታ | መደብ |
|---|---|---|---|
| ውእቱ/ዝኩ/ዝክቱ/ዝስኩ | ውእቶሙ/እሙንቱ/እልኩ/እልክቱ | ተባዕት | ፫ኛ |
| ይእቲ/እንታክቲ/እንትኩ | ውእቶን/እማንቱ/እልኮን/እልክቶን | አንስት | |

አመልካቾች ከሰዋስው አንፃር በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፦

፩· አመልካች ተውላጠ ሥም

፪· አመልካች ቅጽል

፩· **አመልካች ተውላጠ ሥም፦** ማለት ከአመልካቹ ቀጥሎ ሥም መግባቱ (መከተሉ) ቀርቶ ማሰሪያ አንቀጽ ተከትሎ ሲመጣ የሚታይ ሰዋስዋዊ ሂደት ነው፡፡ በአጭሩ አመልካች ቅጽል ማለት ማሰሪያ አንቀጽ ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፦ <u>ዝንቱ</u> ወልድ መጽዐ እም ኀሬ፡፡ ማለቱ ቀርቶ ⟹ (አመልካች + ሥም + ማሰሪያ አንቀጽ)

<u>ዝንቱ</u> መጽዐ እም ኀሬ፡፡ ወይም ⟹ (አመልካች + ማሰሪያ አንቀጽ)

<u>**መጽዐ**</u> እም ኀሬ፡፡ ማሰሪያ አንቀጽ ብቻ

ከላይ የቀረበውን ምሳሌ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተተነተነውን ተመልከቱ፡፡

| ተራ ቁ | አመልካች | ሥም | ማሰሪያ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ዝንቱ | ወልድ | መጽዐ | የተሰጠ መደበኛ ዐረፍተ ነገር |
| ፪ | ዝንቱ | – | መጽዐ | አመልካቹ ማሰሪያውን አስከትሏል |
| ፫ | – | – | መጽዐ | ዝንቱን በውስጠ ታዋቂነት ይዟል |

፪· **አመልካች ቅጽል፡-** ማለት ስምን ቀድሞ በመግባት ወይም ሥምን በማስከተል እያገላመሰ የሚሄድ ሰዋስዋዊ ሂደት ነው፡፡

**ምሳሌ፦** <u>ውእቶሙ</u> አበው መሀሩነ ሥርዓተ አምልኮ፡፡ <u>ውእቶሙ</u> የሚለው አመልካች ቅጽል <u>አበው</u> የሚለውን ሥም በግልጽ አስቀምጦ አገላምሶታል፡፡

<u>እማንቱ</u> አንስት ሖራ ኀበ ደብረ ከርቤ፡፡ <u>እማንቱ</u> የሚለው አመልካች ቅጽል <u>አንስት</u> የሚለውን ሥም አገላምሶታል፡፡

<u>እሙንቱ</u> እደው ያፈቅሩኒ ጥቀ፡፡ <u>እሙንቱ</u> ያለው አመልካች ቅጽል <u>የእደው</u> አገላማሽ ነው፡፡

## ፪·፫· አገናዛቢዎች (Possessives)

*“አገናዘበ”* የሚለው አመሳከረ አረጋገጠ የሚል አቻ ትርጉም ሲኖረው አገናዛቢ ማለት የኔነትን ወይም የአንድን ነገር ባለንብረትነትን ባለቤትነትን የሚገልጽ ክፍለ - ሰዋስው ነው፡፡ አገናዛቢዎች በአጠቃላይ በሦስት ይመደባሉ፡፡ እነሱም፦

ሀ· አገናዛቢ ተውላጠ ሥም (Possessive Pronoun)

ለ· አጋናዛቢ ቅጽል (Possessive Adjective)

ሐ· አገናዛቢ አጸፋ (Possessive Reflexive) በመባል ይታወቃሉ፡፡

**ሀ· አገናዛቢ ቅጽሎች፡-** ከሌላ ሥም ጋር ሳይጣመሩ ራሳቸው እንደባለቤትና እንደመሙያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

**፩· በሥም ሲያገናዝብ**

ሥም "**እም**"

| | | ቅጥያ (ዝርዝር) |
|---|---|---|
| አነ | እምየ | የ |
| ንሕነ | እምነ | ነ |
| አንተ | እምከ | ከ |
| አንቲ | እምኪ | ኪ |
| አንትሙ | እምክሙ | ክሙ |
| አንትን | እምክን | ክን |
| ውእቱ | እሙ | ኡ |
| ይእቲ | እማ | ኣ |
| ውእቶሙ | እሞሙ | ኦሙ |
| ውእቶን | እሞን | ኦን |

**፪· በመስተዋድድ ሲያገናዝብ**

መስተዋድድ "**ምስለ**"

| | | ቅጥያ (ዝርዝር) |
|---|---|---|
| አነ | ምስሌየ | የ |
| ንሕነ | ምስሌነ | ነ |
| አንተ | ምስሌከ | ከ |
| አንቲ | ምስሌኪ | ኪ |
| አንትሙ | ምስሌክሙ | ክሙ |
| አንትን | ምስሌክን | ክን |
| ውእቱ | ምስሌሁ | ሁ |
| ይእቲ | ምስሌሃ | ሂ |
| ውእቶሙ | ምስሌሆሙ | ሆሙ |
| ውእቶን | ምስሌሆን | ሆን |

**፫· በጥሬ ዘር**

ጥሬ ዘር "**ቅዳሴ**"

| | | ቅጥያ (ዝርዝር) |
|---|---|---|
| አነ | ቅዳሴየ | የ |
| ንሕነ | ቅዳሴነ | ነ |
| አንተ | ቅዳሴከ | ከ |
| አንቲ | ቅዳሴኪ | ኪ |
| አንትሙ | ቅዳሴክሙ | ክሙ |
| አንትን | ቅዳሴክን | ክን |
| ውእቱ | ቅዳሴሁ | ሁ |
| ይእቲ | ቅዳሴሃ | ሂ |
| ውእቶሙ | ቅዳሴሆሙ | ሆሙ |
| ውእቶን | ቅዳሴሆን | ሆን |

***ማስታወሻ፦*** በመስተዋድድና በጥሬ ዘር ጊዜ ለውእቱ "ሁ" ፣ ለይእቲ "ሃ" ፣ ለውእቶሙ "ሆሙ" እና ለውእቶን "ሆን" በዝርዝርነት እንደተቀጸሉ አስተውል።

**ለ· አገናዛቢ ተውላጠ ሥም፦** አገናዛቢ ተውላጠ ሥሞች የሚባሉት ባለቤትነትን/ባለንብረትነትን የሚያመለክቱ የሥም ገላጮች ናቸው። እነዚህም በዘ፣ በእለ፣ በእንተ የሚዘረዘሩ ሲሆኑ እኔ፣ የኔ፣ የኔው፣ የኔዋ፣ የኔይቱ እና የኔዎቹ የሚል ትርጉም ያመጣሉ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አነ | ዚአየ | እንቲአየ | እሊአየ | የእኔ | Mine |
| ንሕነ | ዚአነ | እንቲአነ | እሊአነ | የእኛ | Ours |
| አንተ | ዚአከ | እንቲአከ | እሊአከ | የአንተ | Yours |
| አንቲ | ዚአኪ | እንቲኪ | እሊአኪ | የአንቺ | Yours |
| አንትሙ | ዚአክሙ | እንቲአክሙ | እሊአክሙ | የእናንተ | Yours |
| አንትን | ዚአክን | እንቲአክን | እሊአክን | የእናንተ (አንስት) | Yours |
| ውእቱ | ዚአሁ | እንቲአሁ | እሊአሁ | የእሱ | His |
| ይእቲ | ዚአሃ | እንቲአሃ | እሊአሃ | የእሷ | Hers |
| ውእቶሙ | ዚአሆሙ | እንቲአሆሙ | እሊአሆሙ | የእነሱ | Theirs |
| ውእቶን | ዚአሆን | እንቲአሆን | እሊአሆን | የእነሱ (አንስት) | Theirs |

**ሐ· አገናዛቢ አጸፋዎች፦** በዐረፍተ ነገር ውስጥ እንደ ባለቤትና ተሳቢ ሆነው ይገባሉ በአገናዛቢ ቅጽሎች ላይ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን የሚያመለክቱ ድህረ ግንድ ቅጥያ በመጨመር ይመሰረታሉ።

**ምሳሌ፦** ዝንቱ ውእቱ **<u>ወልድየ</u>**።

ማርያም ድንግል **<u>እምነ</u>** ይእቲ።

ሳራ ይእቲ **<u>በእሲቱ</u>** ለአብርሃም

***<u>ማስታወሻ፦</u>*** አጸፋ የሚባሉት የእኔ የእራሴ፣ የእኛ የእራሳች በእንግሊዝኛው My Self, Our Selves እያሉ የሚሄዱት ናቸው። በሚከተለው መልክ ሲገለፁም ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| ለሊየ | ሊተ |
| ለሊነ | ለነ |
| ለሊከ | ለከ |
| ለሊኪ | ለኪ |
| ለሊክሙ | ለክሙ |
| ለሊክን | ለክን |
| ለሊሁ | ሎቱ |
| ለሊሃ | ላቲ |
| ለሊሆሙ | ሎሙ |
| ለሊሆን | ሎን |

# ቃለ ተዋስዖ

| በላይነሽ | ጌታቸው |
|---|---|
| ሠላም ለከ እኍየ | ወሠላም ለኪ እኅትየ |
| መኑ ውእቱ ሥምከ | ሥምየ ውእቱ ጌታቸው |
| መኑ ውእቱ ሥመ አቡከ | ሥመ አቡየ ውእቱ ወልዴ |
| መኑ ውእቱ ሥመ እምከ | ሥመ እምየ ውእቱ ማለፊያ |
| እስፍንቱ ውእቱ አዝማኒከ | አዝማንየ ውእቱ እሥራ ወስድስተ |
| እም አይቴ መጻዕከ | እም ደብረ ታቦር |
| ኀበ አይቴ ትሐውር | አነ እሄሉ ዝየ |
| ምንተ ትገብር ዝየ | እትመሀር ትምህርተ |
| አይቴ ትትመሀር | ውስተ አዲስ አበባ መካነ አእምሮ |
| ምንተ ትትመሀር | ህክምና |
| በል ሰናይ መዓልት | ኦሆ እኅትየ ለኩልነ |

## ምዕራፍ ሦስት

## ፫. ግስ

## ፫.፩. ትርጓሜ ግስ

መምህር አፈወርቅ ተክሌ “በግእዝ ገሰሰ፣ ገሲስ/ሶት፣ ይገስስ፣ ይግስስ በዕብራይስጥ ጋሻሽ፣ በሱርስት ጋሻ በዐረቢኛ ጀስ፣ በአምርኛ መዳሰስ፣ መዳበስ፣ በእጅ መንካት፣ ማባበስ፣ መያዝ መጨበጥ ማለት ነው። አንድም ግስ ማለት የቅኔ፣ የዚቅ፣ የወረብ፣ የለዘበ መገሰስ አንዱን ቃል ማርባት፣ ማብዛት፣ የሩቅን ለቅርብ፣ የወንድን ለሴት፣ ያንዱን ለብዙ መስጠት፣ ማወራረስ፣ የጥፈት፣ የፍርድ፣ የገንዘብ፣ የክብር መፋቅ፣ መፈቅፈቅ፣ መሚሰስ፣ መጥፋት፣ መደምሰስ፣ መለወጥ መገልበጥ ለማለት ይነገራል። አንድም ግስ ማለት እክት፣ ጓዝ፣ ግስንግስ፣ ዕቃ፣ ግሴት፣ የሚጋዝና የሚዳሰስ ሁሉ። ሰማይ ከነግሡ ምድር ከነ ጓዙ እንዲሉ ከነጓዙ ለማለት። ጋሰስ፣ አጋሰስ ማለት ከዚህ ወጥቷል። አንድም ግስ በቁሙ የቋንቋ መጣፍ የዘርና የነባር መደብ መዝገበ ቃል ንባቡ በፊደል ተራ የታከተ የተከተተ ምሥጢሩ ግን ተወራራሽ ቃል ማለት ነው። አንዱ አንቀጽ እስከ ሰማንያ ገባሩና ጥሬው አስከ አስር መርባቱ በመወራረሻ ነው።” ብለውታል። (መጽሐፈ ታሪክ ወግሥ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም አ.አ ገጽ ፰፭)። በሌላ ትርጉም ግስ ማለት የንግግር መቋጠሪያ፣ የዐረፍተ ነገር ማሠሪያ፣ የጽሕፈት መዝጊያ የድርጊት መግለጫ ከክፍላተ ቃላት አንዱና ዋነኛው ነው።

## ፫.፪. አርእስተ ግስ

አርእስተ ግስ የተባሉት ፰ት ወገን ናቸው እነሱም፦

| | | |
|---|---|---|
| ፩. ቀተለ | ፭. ማሕረከ | ናቸው። |
| ፪. ቀደሰ | ፮. ሴሰየ | |
| ፫. ተንበለ | ፯. ክህለ | |
| ፬. ባረከ | ፰. ጦመረ | |

## ፫.፫. የረብሐ ግስ መንገዶች

የረብሐ ግስ መንገዶች ፲፰ት ናቸው። እነሱም፦

| ትልቅ | የረብ ግስ መንገዶች | | ግስ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ቀዳማይ አንቀጽ (ኃላፊ፣ ግስ፣ ዘማች) | | ቀተለ |
| ፪ | ካልአይ አንቀጽ (ትንቢት) | | ይቀትል |
| ፫ | ዘንድ አንቀጽ | | ይቅትል |
| ፬ | ትዕዛዝ | | ይቅትል |
| ፭ | ንኡስ አንቀጽ | | ቀቲል/ሎት |
| ፮ | ሳልስ ቅጽል | ተባዕት | ቀታሊ |
| ፯ | በብዙ | | ቀታሊያን |
| ፰ | ሳልስ ቅጽል | አንስት | ቀታሊት |
| ፱ | በብዙ | | ቀታሊያት |
| ፲ | ሳድስ ቅጽል | ተባዕት | ቅቱል |
| ፲፩ | በብዙ | | ቅቱላን |
| ፲፪ | ሳድስ ቅጽል | አንስት | ቅትልት |
| ፲፫ | በብዙ | | ቅቱላት |
| ፲፬ | ባዕድ ቅጽል | ተባዕት | መቅትል፣ መስተቅትል፣ መስተቃትል |
| ፲፭ | በብዙ | | መቅትላን፣ መስተቅትላን፣ መስተቃትላን |
| ፲፮ | ባዕድ ቅጽል | አንስት | መቅትልት፣ መስተቅትልት፣ መስተቃትልት |
| ፲፯ | በብዙ | | መቅትላት፣ መስተቅትላት፣ መስተቃትላት |
| ፲፰ | መድበል | | ቀተልት |

የረብሐ ግስ መንገዶችን ካየን በኋላ ከረብሐ ግስ በፊት የግስን አዋጅ ማየት ያስፈልጋል ምክንያቱም ግስ በምናረባበት ጊዜ የምናረባቸው ግሶች የሚከተሉትን ሰዋስዋዊ ሕግ ቀድሞ ማወቅ በ፲፰ቱ የረብሐ ግስ መንገዶች ሳይቸገሩ ለማርባት ይረዳልና። አንባቢያን በተቻላቸው መጠን አንብበው በቃላቸው ለመያዝና ምሳሌዎችን እየጨመሩ እንዲያዩ እመክራለሁ። በዚህ የግስ አዋጅ ውስጥ የምናየው ግሶች በርባታ ጊዜ ከአርዕስተ ግሶች ጋር ያላቸውን ዝምድናና ተመሳሳይነት ነው። ምክንያቱም ሁሉንም ግሶች ለማርባት ጊዜም ቦታም በሰፊው ስለሚጠይቅ መሰረታውያኑን ማወቅና ማሳወቅ ከሀ እስከ ፐ ያሉ ግሶችን የርባታ ሁኔታ ለመረዳ ስለሚያስችለን አዋጁን እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ።

## ፫.፬. የግስ አዋጅ

፩. ከላይ የተጠቀሱት የግስ አርእስት ራስ ራሳቸውን ከመሳሰሉ ሠራዊታቸው በተጨማሪ ሌላ አመል ያላቸው ሠራዊት አሏቸው የቀተለ ሠራዊት ሦስት ናቸው እነሱም ሀቤተ ተኬሰ ሰኮተ ናቸው የቀደሰ ሠርዌ ግን አንድ አንገለገ ብቻ ነው የተንበለ ሠራዊት ሦስት ናቸው ማን ማን ናቸው ቢሉ ቀብያውበጠ ቀንጦሰጠ ዜርዜቀ ናቸው የባረከና የክህለ ግን ራስ ራሳቸውን ከመሳሰሉት በስተቀር ሌላ አመል ያላቸው ሠራዊት አይገኙላቸውም የማሕረከ ሠራዊት ሦስት ናቸው እነሱስ ማን ማን ናቸው ቢሉ አንቃዕደዎ ሰካዕለዎ አናሕሰየ ናቸው የሴሰየ ሠራዊት ሦስት ናቸው እነሱስ ማን ማን ናቸው ቢሉ አሌለየ አንጌገየ አቅዜዘየ ናቸው፣ የጦመረ ሠራዊት አራት ናቸው እነሱስ ማን ማን ናቸው ቢሉ አልሆሰሰ አክሞሰሰ ሶርዔመ ኀርዔመ ናቸው። እነዚህ ስምንቱ ግሶች ከነ ሠራዊታቸው እንደሚከተለው ተጠቃለዋል።

| ተራ ቁ | አርእስት | ሠራዊት | ፍች |
|---|---|---|---|
| ፩ | ቀተለ | ኀቤተ | አገለገለ |
| | | ተኬሰ | መታ |
| | | ሰኮተ | ወለወለ |
| ፪ | ቀደሰ | አንገለገ | አከማቸ |
| ፫ | ተንበለ | ቀብያውበጠ | ቀላወጠ |
| | | ቀንጦሰጠ | ተሰለፈ |
| | | ዜርዜቀ | ነፋ |
| ፬ | ባረከ | አልቦ | |
| ፭ | ማሕረከ | ሰካዕለወ | ቆጠቆጠ |
| | | አንቃዕደወ | አንጋጠጠ |
| | | አናሕሰየ | አቃለለ |
| ፮ | ሴሰየ | አሌለየ | ማለደ |
| | | አቅዜዘየ | ቅዝዝ ቀዝዝ አለ |
| | | አንጌገየ | ተቅበዘበዘ |
| ፯ | ክህለ | አልቦ | |
| ፰ | ጦመረ | አልኆሰሰ | ሹክ ሹክ አለ |
| | | አክሞሰሰ | ፍግግ ፍግግ አለ |
| | | ሶርዔመ | ለምድ አወጣ |
| | | ኀርዔመ | አገመ |

፪. የግስ መነሻ ቀለማት አምስት ናቸው እነሱም ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስና ሳብዕ ናቸው። ለዚሁም ማስረጃ በግዕዝ፡ ቀተለ፣ ቀደሰ፣ ተንበለ፣ በራብዕ፡ ባረከ፣ ማሕረከ፣ በኃምስ፡ ሴሰየ፣ በሳድስ፡ ክህለ፣ በሳብዕ፡ ጦመረ ናቸው። በካዕብና በሳልስ የሚነሳ ግስ የለም ለዚሁም ማስረጃ ሖረ ቴሀ ይላል እንጂ ሑረ ቲሀ አይልም።

፫. የግስ መድረሻ ቀለማት ሁለት ናቸው እነሱስ ማን ማን ናቸው ቢሉ ግእዝና ኃምስ ናቸው በግእዝ ከሀ እስከ ፐ ያሉ ግሶች ሲሆኑ በኃምስ ግን አንድ ይቤ ብቻ ነው። ይቤማ ነባር አንቀጽ አይደለምን ቢሉ ካልዓዩን ዘንዱን ትዕዛዙን ይዞ በመገኘቱ ግስ ከአበይት አናቅጽ ውጪ የረብሐ ግስ፣ መንገድ ባለመከተሉ ነባር አንቀጽ ተብሏል።

፬. ሁለት ቀለም ሆኖ በግእዝ ተነስቶ በግእዝ የደረሰ ቀለሙ የጠበቀ መረን ቈረን ነደን ጠበን የመሳሰለ ግስ በቀተለ ቤት ይወርዳል።

፭. ሁለት ቀለም ሆኖ በኃምስ ተነስቶ በግእዝ የደረሰ ቀለሙ የላላ ሔመን ዔለን ዔመን የመሳሰለ ግስ በቀተለ ቤት ይወርዳል በካልዓዩ ይን ይጨምራል ዘንድና ትዕዛዙ በሳልስ ይዘምታል ንዑስ አንቀጹ ሳድስ እንጂ ሳልስ አይሆንም።

፮. ሁለት ቀለም ሆኖ በሳብዕ ተነስቶ በግእዝ የደረሰ ቀለሙ የላላ ሖረን ቆመን ጾመን የመሳሰለ ግስ በቀተለ ቤት ይወርዳል በካልዓዩ ውን ይጨምራል ዘንድና ትእዛዙ በካዕብ ይዘምታል ንዑስ አንቀጹ እንደ ቀተለ ሳድስ ቅጽሉ እንደ ቀደሰ ነው።

፯. በቀተለ ቤት በወ በክህለ ቤት በው የሚነሳ ግስ ሁሉ ዘንድና ትዕዛዙ ይዘልቃልም ይጎርዳልም። በቀተለ ቤት የወ ማስረጃ ወለደ ብሎ ይወልድ ይውልድ ይውልድ ይላል ይኼውም ሲዘልቅ ነው ሲጎርድ ግን ወለደ ብሎ ይወልድ ይለድ ይለድ ይላል። በክህለ ቤት የው ማስረጃ ውህደ ብሎ ይውህድ ይወህድ ይወህድ ይላል ይኼውም ሲዘልቅ ነው ሲጎርድ ግን ውህደ ብሎ ይውህድ ይህድ ይህድ ይላል።

፰. በቀተለ ቤት ሀ እና አ መድርሻ የሆኑበት ግስ ሁሉ ዘንድና ትዕዛዙ በባረከ አመል ይዘምታል ማለት የዘንድና የትዕዛዙ ሥርዎ ቀለም ቀድመ መድረሻ ራብዕ ይሆናል። ለዚሁም ማስረጃ መርሐ ብሎ ይመርሕ ይምራሕ ይምራሕ መጽአ ብሎ ይመጽእ ይምጻእ ይምጻእ ይላል።

፱. በቀተለ ቤት ሀ እና አ ተደራርበው መነሻ የሆኑበት ግስ የዘንድና የትዕዛዙ ሥርዎ ቀለም ፍጹም ግእዝ ይሆናል ለዚሁም ማስረጃ አሀረ ብሎ ይእህር ይአህር ይአህር፣ አሀዘ ብሎ ይእህዝ ይአህዝ ይአህዝ፣ አሀደ ብሎ ይእህድ ይአህድ ይአህድ ይላል።

፲. በቀተለ ቤት ወ እና የ በመካከሉ ያሉበት ግስ ዘንድና ትዕዛዙ ይዘልቃልም ይጎርዳልም ለዚህም የወ ማስረጃ ሀወለ ብሎ ይሀውል ይሀውል ይሀውል ይላል ይኼውም ሲዘልቅ ነው ሲጎርድ ግን ሀወለ ብሎ ይሀውል ይሁል ይሁል ይላል የየ ማስረጃ ሀየሰ ብሎ ይሀይስ ይሀይስ ይሀይስ ይላል ይኼውም ሲዘልቅ ነው ሲጎርድ ግን ሀየሰ ብሎ ይሀይስ ይሂስ ይሂስ ይላል።

፲፩. በቀደሰ ቤት በሀ እና በአ የሚነሱ ግሶች የዘንድና የትዕዛዝ ሥርዎ ቀለማቸው ፍጹም ግእዝ ይሆናል ለዚሁም የሀ ማስረጃ ኀየለ ብሎ ይኄይል ይኀይል ይኀይል፣ የአ ማስረጃ አዘዘ ብሎ ይኤዝዝ ይአዝዝ ይአዝዝ ይላል።

፲፪. ወ እና የ መድረሻ የሆኑበት ግስ ካልዓዩ ዘንድና ትዕዛዙ ይጎርዳል እንጂ አይዘልቅም ለዚሁም የወ ማስረጃ ሀለወ ብሎ ይሄሉ ይሀሉ ይሀሉ ለበወ ብሎ ይሌቡ ይለቡ ይለቡ ይላል። የየ ማስረጃ ሰነየ ብሎ ይሴኒ ይሰኒ ይሰኒ ጸለየ ብሎ ይጼሊ ይጸሊ ይጸሊ ይላል።

፲፫. ወ እና የ መድረሻ የሆኑበት ግስ ደጊመ ቃል ካለው ይዘልቃል እንጂ አይጎርድም ለዚሁም ***የወ*** ማስረጃ ***ሌወወ*** ብሎ ***ይሌውው ይሌውው ይሌውው፣ ጼወወ*** ብሎ ***ይጼውው ይጼውው ይጼውው*** ይላል ***የየ*** ማስረጃ ***ጻሕየየ*** ብሎ ***ይጻሐይይ ይጻሕይይ ይጻሕይይ፣ ጸማሕየየ*** ብሎ ***ይጸመሐይይ ይጸማሕይይ ይጸማሕይይ*** ይላል።

## ፫.፳. ረብሐ ግስ ዘሰመንቱ

**፩· ቀተለ**

| ግስ | አማርኛ |
|---|---|
| ቀተለ | ገደለ |
| ይቀትል | ይገድላል |
| ይቅትል | ይገድል ዘንድ |
| ይቅትል | ይግደል |
| ቀቲል/ሎት | መግደል |
| ቀታሊ | የገደለ |
| ቀታሊያን | የገደሉ (ተባዕት) |
| ቀታሊት | የገደለች |
| ቀታሊያት | የገደሉ (አንስት) |
| ቅቱል | የተገደለ |
| ቅቱላን | የተገደሉ (ተባዕት) |
| ቅትልት | የተገደለች |
| ቅቱላት | የተገደሉ (አንስት) |
| መቅትል፣ መስተቅትል፣ መስተቃትል | የተገደለ |
| መቅትላን፣ መስተቅትላን፣ መስትቃትላን | የተገደሉ (ተባዕት) |
| መቅትልት፣ መስተቅትልት፣ መስትቃትልት | የተገደለች |
| መቅትላት፣ መስተቅትላት፣ መስተቃትላት | የተገደሉ (አንስት) |
| ቀተልት | ገዳዮች |

ቀተለን የመሰለ ግስ “ፈጠረ”

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ፈጠረ | ፈጠረ |
| ይፈጥር | ይፈጥራል |
| ይፍጥር | ይፈጥር ዘንድ |
| ይፍጥር | ይፍጠር |
| ፈጢር/ሮት | መፍጠር |
| ፈጣሪ | የፈጠረ |
| ፈጣሪያን | የፈጠሩ (ተባዕት) |
| ፈጣሪት | የፈጠረች |
| ፈጣሪያት | የፈጠሩ (አንስት) |
| ፍጡር | የተፈጠረ |
| ፍጡራን | የተፈጠሩ (ተባዕት) |
| ፍጥርት | የተፈጠረች |
| ፍጡራት | የተፈጠሩ (አንስት) |
| መፍጥር፣ መስተፍጥር፣ መስተፋጥር | የተፈጠረ |
| መፍጥራን፣ መስተፍጥራን፣ መስተፋጥራን | የተፈጠሩ (ተባዕት) |
| መፍጥርት፣ መስተፍጥርት፣ መስተፋጥርት | የተፈጠረች |
| መፍጥራት፣ መስተፍጥራት፣ መስተፋጥራት | የተፈጠሩ (አንስት) |
| ፈጠርት | የፈጠሩ |

፪. ቀደሰ

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ቀደሰ | አመሰገነ |
| ይቄድስ | ያመሰግናል |
| ይቀድስ | ያመሰግን ዘንድ |
| ይቀድሰ | ያመስግን |
| ቀድሶ/ት | ማመስገን |
| ቀዳሲ | ያመሰገነ |
| ቀዳሲያን | ያመሰገኑ (ተባዕት) |
| ቀዳሲት | ያመሰገነች |
| ቀዳሲያት | ያመሰገኑ (አንስት) |
| ቅዱስ | የተመሰገነ |
| ቅዱሳን | የተመሰገኑ (ተባዕት) |
| ቅድስት | የተመሰገነች |
| ቅዱሳት | የተመሰገኑ (አንስት) |
| መቀድሰ፣ መስተቀድስ፣ መስተቃድስ | የተመሰገነ |
| መቀድሳን፣ መስተቀድሳን፣ መስተቃድሳን | የተመሰገኑ (ተባዕት) |
| መቀድስት፣ መስተቀድስት፣ መስተቃድስት | የተመሰገነች |
| መቀድሳት፣ መስተቀድሳት፣ መስትቃድሳት | የተመሰገኑ (አንስት) |
| ቀደስት | አመስጋኞች |

ቀደሰን የመሰለ ግስ “ወደሰ”

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ወደሰ | አመሰገነ |
| ይዌድስ | ያመሰግናል |
| ይወድስ | ያመሰግን ዘንድ |
| ይወድስ | ያመስግን |
| ወድሶ/ት | ማመስገን |
| ወዳሲ | ያመሰገነ |
| ወዳሲያን | ያመሰገኑ (ተባዕት) |
| ወዳሲት | ያመሰገነች |
| ወዳሲያት | ያመሰገኑ (አንስት) |
| ውዱስ | የተመሰገነ |
| ውዱሳን | የተመሰገኑ (ተባዕት) |
| ውድስት | የተመሰገነች |
| ውዱሳት | የተመሰገኑ (አንስት) |
| መወድስ፣ መስተወድስ፣ መስተዋድስ | የተመሰገነ |
| መወድሳን፣ መስተወድሳን፣ መስትዋድሳን | የተመሰገኑ (ተባዕት) |
| መወድስት፣ መስተወድስት፣ መስተዋድስት | የተመሰገነች |
| መወድሳት፣ መስትወድሳት፣ መስተዋድሳት | የተመሰገኑ (አንስት) |
| ወደስት | አመስጋኞች |

### ፫· ተንበለ

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ተንበለ | ለመነ |
| ይተነብል | ይለምናል |
| ይተንብል | ይለምን ዘንድ |
| ይተንብል | ይለምን |
| ተንብሎ/ት | መለመን |
| ተንባሊ | የለመነ |
| ተንባሊያን | የለመኑ (ተባዕት) |
| ተንባሊት | የለመነች |
| ተንባሊያት | የለመኑ (አንስት) |
| ትንቡል | የተለመነ |
| ትንቡላን | የተለመኑ(ተባዕት) |
| ትንብልት | የተለመነች |
| ትንቡላት | የተለመኑ (አንስት) |
| መተንብል፣ መስተተንብል፣ መስተተናብል | የተለመነ |
| መተንብላን፣ መስተተንብላን፣ መስተተናብላን | የተለመኑ (ተባዕት) |
| መተንብልት፣ መስተተንብልት፣ መስተተናብልት | የተለመነች |
| መተንብላት፣ መስተተንብላት፣ መስተተናብላት | የተለመኑ (አንስት) |
| ተንብልት | ለማኞች |

ተንበለን የመሰለ ግስ “ደንገጸ”

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ደንገጸ | ደነገጠ |
| ይደነግጽ | ይደነግጣል |
| ይደንግጽ | ይደነግጥ ዘንድ |
| ይደንግጽ | ይደንግጥ |
| ደንግጾ/ት | መደንገጥ |
| ደንጋጺ | የደነገጠ |
| ደንጋጺያን | የደነገጡ (ተባዕት) |
| ደንጋጺት | የነገጠች |
| ደንጋጺያት | የደነገጡ (አንስት) |
| ድንጉጽ | የተደነገጠ |
| ድንጉጻን | የተደነገጡ (ተባዕት) |
| ድንግጽት | የተደነገጠች |
| ድንጉጻት | የተደነገጡ (አንስት) |
| መደንግጽ፣ መስተደንግጽ፣ መስተደናግጽ | የተደነገጠ |
| መደንግጻን፣ መስተደንግጻን፣ መስተደናግጻን | የተደነገጡ (ተባዕት) |
| መደንግጽት፣ መስተደንግጽት፣ መስተደናግጽት | የተደነገጠች |
| መደንግጻት፣ መስተደንግጻት፣ መስተደናግጻት | የተደነገጡ (አንስት) |
| ደንገጽት | ደንጋጮች |

፬· ባረከ

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ባረከ | ባረከ |
| ይባርክ | ይባርካል |
| ይባርክ | ይባርክ ዘንድ |
| ይባርክ | ይባርክ |
| ባርኮ/ት | መባረክ |
| ባራኪ | የባረከ |
| ባራኪያን | የባረኩ(ተባዕት) |
| ባራኪት | የባረከች |
| ባራኪያት | የባረኩ (አንስት) |
| ቡሩክ | የተባረከ |
| ቡሩካን | የተባረኩ (ተባዕት) |
| ቡርክት | የተባረከች |
| ቡሩካት | የተባረኩ (አንስት) |
| መባርክ፣ መስተባርክ | የተባረከ |
| መባርካን፣ መስተባርካን | የተባረኩ (ተባዕት) |
| መባርክት፣ መስተባርክት | የተባረከች |
| መባርካት፣ መስተባርካት | የተባረኩ (አንስት) |
| ባረክ/ት | ባራኪዎች |

ባረከን የመሰለ ግስ “**ላቀሰ**”

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ላቀሰ | አለቀሰ |
| ይላቅስ | ያለቅሳል |
| ይላቅስ | ያለቅስ ዘንድ |
| ይላቅስ | ያልቅስ |
| ላቅሶ/ት | ማልቅስ |
| ላቃሲ | ያለቀሰ |
| ላቃሲያን | ያለቀሱ (ተባዕት) |
| ላቃሲት | ያለቀሰች |
| ላቃሲያት | ያለቀሱ (አንስት) |
| ሉቁስ | የተለቀሰ |
| ሉቁሳን | የተለቀሱ (ተባዕት) |
| ሉቅስት | የተለቀሰች |
| ሉቁሳት | የተለቀሱ (አንስት) |
| መላቅስ፣ መስተላቅስ | የተለቀሰ |
| መላቅሳን፣ መስተላቅሳን | የተለቀሱ (ተባዕት) |
| መላቅስት፣ መስተላቅስት | የተለቀሰች |
| መላቅሳት፣ መስተላቅሳት | የተለቀሱ (አንስት) |
| ላቀስት | አልቃሾች |

## ፰· ማሕረከ

| ግእዝ | አማርኛ |
| --- | --- |
| ማሕረከ | ማረከ |
| ይመሐርክ | ይማርካል |
| ይማሕርክ | ይማርክ ዘንድ |
| ይማሕርክ | ይማርክ |
| ማሕርኮ/ት | መማረክ |
| ማሕራኪ | የማረከ |
| ማሕራኪያን | የማረኩ (ተባዕት) |
| ማሕራኪት | የማረከች |
| ማሕራኪያት | የማረኩ (አንስት) |
| ምሕሩክ | የተማረከ |
| ምሕሩካን | የተማረኩ (ተባዕት) |
| ምሕርክት | የተማረከች |
| ምሕሩካት | የተማረኩ (አንስት) |
| መማሕርክ፣ መስተማሕርክ፣ መስተማሓርክ | የተማረከ |
| መማሕርካን፣ መስተማሕርካን፣ መስተማሓርካን | የተማረኩ (ተባዕት) |
| መማሕርክት፣ መስተማሕርክት፣ መስተማሓርክት | የተማረከች |
| መማሕርካት፣ መስተማሕርካት፣ መስተማሓርካት | የተማረኩ (አንስት) |
| ማሕረክ/ት | ማራኪዎች |

ማሕረከን የመሰለ ግስ “ዳሕመመ”

| ግእዝ | አማርኛ |
| --- | --- |
| ዳሕመመ | አፈረሰ |
| ይደሐምም | ያፈርሳል |
| ይዳሕምም | ያፈርስ ዘንድ |
| ይዳሕምም | ያፍርስ |
| ዳሕምሞ/ት | ማፍረስ |
| ዳሕማሚ | ያፈረሰ |
| ዳሕማሚያን | ያፈረሱ (ተባዕት) |
| ዳሕማሚት | ያፈረሰች |
| ዳሕማሚያት | ያፈረሱ (አንስት) |
| ድሑሙም | የፈረሰ |
| ድሑሙማን | የፈረሱ (ተባዕት) |
| ድሕምምት | የፈረሰች |
| ድሑሙማት | የፈረሱ (አንስት) |
| መዳሕምም፣ መስተዳሕምም፣ መስተዳሓምም | የፈረሰ |
| መዳሕምማን፣ መስተዳሕምማን፣ መስተዳሓምማን | የፈረሱ (ተባዕት) |
| መዳሕምምት፣ መስተዳሕምምት፣ መስተዳሓምምት | የፈረሰች |
| መዳሕምማት፣ መስተዳሕምማት፣ መስተዳሓምማት | የፈረሱ (አንስት) |
| ዳሕመምት | ፈራሾች |

፮. ሴሰየ

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ሴሰየ | መገበ |
| ይሴሲ | ይመግባል |
| ይሴሲ | ይመግብ ዘንድ |
| ይሴሲ | ይመግብ |
| ሴስዮ/ት | መመገብ |
| ሴሳዪ | የመገበ |
| ሴሳዪያን | የመገቡ (ተባዕት) |
| ሴሳዪት | የመገበች |
| ሴሳዪያት | የመገቡ (አንስት) |
| ሲሱይ | የተመገበ |
| ሲሱያን | የተመገቡ (ተባዕት) |
| ሲሲት (ሲስይት) | የተመገበች |
| ሲሱያት | የተመገቡ (አንስት) |
| መሴስይ፣ መስተሴስይ፣ መስተሲያስይ | የተመገበ |
| መሴስያን፣ መስተሴስያን፣ መስተሲያስያን | የተመገቡ (ተባዕት) |
| መሴስይት፣ መስተሴስይት፣ መስተሲያስይት | የተመገበች |
| መሴስያት፣ መስተሴስያት፣ መስተሲያስያት | የተመገቡ (አንስት) |
| ሴሰይት | መጋቢዎች |

ሴሰየን የመሰለ ግስ "**ሌለየ**"

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ሌለየ | ለየ |
| ይሌሊ | ይለያል |
| ይሌሊ | ይለይ ዘንድ |
| ይሌሊ | ይለይ |
| ሌልዮ/ት | መለየት |
| ሌላዪ | የለየ |
| ሌላዪያን | የለዩ (ተባዕት) |
| ሌላዪት | የለየች |
| ሌላዪያት | የለዩ (አንስት) |
| ሊሉይ | የተለየ |
| ሊሉያን | የተለዩ (ተባዕት) |
| ሊሊት (ሊልይት) | የተለየች |
| ሊሉያት | የተለዩ (አንስት) |
| መሌልይ፣ መስተሌልይ፣ መስተሊያልይ | የተለየ |
| መሌልያን፣ መስተሌልያን፣ መስተሊያልያን | የተለዩ (ተባዕት) |
| መሌልይት፣ መስተሌልይት፣ መስተሊያልይት | የተለየች |
| መሌልያት፣ መስተሌልያት፣ መስተሊያልያት | የተለዩ (አንስት) |
| ሌለይት | ለይዎች |

## ፮. ክህለ

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ክህለ | ቻለ |
| ይክል | ይችላል |
| ይክህል | ይችል ዘንድ |
| ይክህል | ይቻል |
| ክሂል/ሎት | መቻል |
| ከሃሊ | የቻለ |
| ከሃሊያን | የቻሉ (ተባዕት) |
| ከሃሊት | የቻለች |
| ከሃሊያት | የቻሉ (አንስት) |
| ክሁል | የተቻለ |
| ክሁላን | የተቻሉ (ተባዕት) |
| ክህልት | የተቻለች |
| ክሁላት | የተቻሉ (አንስት) |
| መክህል፣ መስተክህል፣ መስተካህል | የተቻለ |
| መክህላን፣ መስተክህላን፣ መስተካህላን | የተቻሉ (ተባዕት) |
| መክህልት፣ መስተክህልት፣ መስተካህልት | የተቻለች |
| መክህላት፣ መስተክህላት፣ መስተካህላት | የተቻሉ (አንስት) |
| ከህልት | ቻዮች |

ክህለን የመሰለ ግስ "**ብህለ**"

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ብህለ | አለ |
| ይብል | ይላል |
| ይብህል | ይል ዘንድ |
| ይብህል | ይበል |
| ብሂል/ሎት | ማለት |
| በሃሊ | ያለ |
| በሃሊያን | ያሉ (ተባዕት) |
| በሃሊት | ያለች |
| በሃሊያት | ያሉ (አንስት) |
| ብሁል | የተባለ |
| ብሁላን | የተባሉ (ተባዕት) |
| ብህልት | የተባለች |
| ብሁላት | የተባሉ (አንስት) |
| መብህል፣ መስተብህል፣ መስተባህል | የተባለ |
| መብህላን፣ መስተብህላን፣ መስተባህላን | የተባሉ (ተባዕት) |
| መብህልት፣ መስተብህልት፣ መስተባህልት | የተባለች |
| መብህላት፣ መስተብህላት፣ መስተባህላት | የተባሉ (አንስት) |
| በህልት | ባዮች |

### ፳. ጦመረ

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ጦመረ<br>ይጦምር<br>ይጦምር<br>ይጦምር<br>ጦምሮ/ት<br>ጦማሪ<br>ጦማሪያን<br>ጦማሪት<br>ጦማሪያት<br>ጡሙር<br>ጡሙራን<br>ጡምርት<br>ጡሙራት<br>መጦምር፣ መስተጦምር፣ መስተጡዋምር<br>መጦምራን፣ መስተጦምራን፣ መስተጡዋምራን<br>መጦምርት፣ መስተጦምርት፣ መስተጡዋምርት<br>መጦምራት፣ መስተጦምራት፣ መስተጡዋምራት<br>ጦመርት | ጣፈ<br>ይጥፋል<br>ይጥፍ ዘንድ<br>ይጣፍ<br>መጣፍ<br>የጣፈ<br>የጣፉ (ተባዕት)<br>የጣፈች<br>የጣፉ (አንስት)<br>የተጣፈ<br>የተጣፉ (ተባዕት)<br>የተጣፈች<br>የተጣፉ (አንስት)<br>የተጣፈ<br>የተጣፉ (ተባዕት)<br>የተጣፈች<br>የተጣፉ (አንስት)<br>ጣፊዎች |

ጦመረን የመሰለ ግሰ "**ኖለወ**"

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ኖለወ<br>ይኖልው<br>ይኖልው<br>ይኖልው<br>ኖልዎ/ት<br>ኖለዊ<br>ኖላውያን<br>ኖላዊት<br>ኖላውያት<br>ኑልው<br>ኑልዋን<br>ኑልውት<br>ኑልዋት<br>መኖልው፣ መስተኖልው፣ መስተኑዋልው<br>መኖልዋን፣ መስተኖልዋን፣ መስተኑዋልዋን<br>መኖልውት፣ መስተኖልውት፣ መስተኑዋልውት<br>መኖልዋት፣ መስተኖልዋት፣ መስተኑዋልዋት<br>ኖለውት | ጠበቀ<br>ይጠብቃል<br>ይጠብቅ ዘንድ<br>ይጠብቅ<br>መጠበቅ<br>የጠበቀ<br>የጠበቁ (ተባዕት)<br>የጠበቀች<br>የጠበቁ (አንስት)<br>የተጠበቀ<br>የተጠበቁ (ተባዕት)<br>የተጠበቀች<br>የተጠበቁ (አንስት)<br>የተጠበቀ<br>የተጠበቁ (ተባዕት)<br>የተጠበቀች<br>የተጠበቁ (አንስት)<br>ጠባቂዎች |

ከመዝ ተፈፀመ ረብሐ ግስ ዘሰመንቱ፡፡

## ፫·፮. አሥራው ፊደላት

ሠርወ ነቀለ፣ ሥርው ስር፣ አሥራው ስሮች ማለት ሲሆን አሥራው የተባሉ ፊደላት አራት ናቸው። እነሱስ ማን ማን ናቸው ቢሉ ተ፣ ነ፣ አ፣ የ ናቸው። እነዚህ አሥራው ፊደላት በአጠቃላይ በ፲፩ አርዕስት በ፳፮ ሠራዊት የሚነገሩ ሲሆኑ እያንዳንዳቸውም ተ ፳ት አርዕስት ፲፩ ሠራዊት፣ ነ ፩ድ ርዕስ ፫ት ሠራዊት፣ አ ፩ድ ርዕስ ፫ት ሠራዊት እና የ ፫ት አርዕስት ፱ ሠራዊት አላቸው ማለት ነው።

ይህስ እንዴት ነው ቢሉ ተ በአንተ፣ በአንቲ፣ በአንትሙ፣ በአንትን እና በይእቲ፡ ነ በንሕነ፡ አ በአነ፡ የ በውእቱ፣ በውእቶሙ እና በውእቶን የሚነገሩ ሲሆኑ ተ ከይእቲ በስተቀር በ፬ቱ በትእዛዛት አናቀጽ አይገኝም ሌሎቹ ግን በ፫ቱም አናቅጽ (በካልዐይ፣ በዘንድና በትዕዛዝ) የገኛሉ።

እነዚህ ፊደላት አሥራው የተባሉበት ምክንያት በግስ እርባታ ጊዜ በአሥሩ መራሕያን በካልአይ፣ በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ እየገቡ የመራሕያኑንና የግስ እርባታ ኺደትን እያዛመዱ የሚገኙ በቸኞች ፊደላት ሆነው ስለተገኙ እና ከእነዚህ ፊደላት በስተቀር ይህ ዓይነት ተግባር ያለው ሌላ ፊደል ባለመኖሩ ነው።

በሚከተለው ሠንጠርዥ የተሠራውን ምሳሌ ተመልከቱ፤

| ግስ | አሥራው ፊደላት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | ተ ፡ በአንተ፣ በአንቲ፣ በአንትሙ፣ በአንትን እና በይእቲ ሲነገር፦ | | | | |
| መራሕያን | ቀዳማይ | ካልዐይ | ዘንድ | ትዕዛዝ | የአሥራው ብዛት |
| አንተ | ቀተልከ | ትቀትል | ትቅትል | ቅትል | ፲፩ |
| አንቲ | ቀተልኪ | ትቀትሊ | ትቅትሊ | ቅትሊ | |
| አንትሙ | ቀተልክሙ | ትቀትሉ | ትቅትሉ | ቅትሉ | |
| አንትን | ቀተልክን | ትቀትላ | ትቅትላ | ቅትላ | |
| ይእቲ | ቀተለት | ትቀትል | ትቅትል | ትቅትል | |
| | ነ ፡ በንሕነ ሲነገር፦ | | | | ፫ |
| ንሕነ | ቀተልነ | ንቀትል | ንቅትል | ንቅትል | |
| | አ ፡ በአነ ሲነገር፦ | | | | ፫ |
| አነ | ቀተልኩ | እቀትል | እቅትል | እቅትል | |
| | የ ፡ በውእቱ፣ በውእቶሙ እና በውእቶን ሲነገር፦ | | | | ፱ |
| ውእቱ | ቀተለ | ይቀትል | ይቅትል | ይቅትል | |
| ውእቶሙ | ቀተሉ | ይቀትሉ | ይቅትሉ | ይቅትል | |
| ውእቶን | ቀተላ | ይቀትላ | ይቅትላ | ይቅትላ | |

## ፫.፯. አዕማድ

አዕማድ የተባሉ ሁለት ክፍል ያላቸው ሲሆኑ እነሱም ምሉዓንና ህፁፃን ይባላሉ።

ሀ. ምሉዓን አዕማደ አርእስት አምስት ወገን ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ ገባሪ፣ ተገባሪ፣ አግባሪ፣ ተጋባሪ፣ አስተጋባሪ ሲሆኑ በአማርኛም አድራጊ፣ ተደራጊ፣ አስደራጊ፣ ተደራራጊ፣ አደራራጊ ማለት ነው።

ምሳሌ፦

| ግስ | ገባሪ | ተገባሪ | አግባሪ | ተጋባሪ | አስተጋባሪ |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | ቀታሊ | ተቀታሊ | አቅታሊ | ተቃታሊ | አስተቃታሊ |
| ቀደሰ | ቀዳሲ | ተቀዳሲ | አቅዳሲ | ተቃዳሲ | አስተቃዳሲ |
| ፈጠረ | ፈጣሪ | ተፈጣሪ | አፍጣሪ | ተፋጣሪ | አስተፋጣሪ |
| ከሰተ | ከሳቲ | ተከሳቲ | አክሳቲ | ተካሳቲ | አስተካሳቲ |
| ሰበረ | ሰባሪ | ተሰባሪ | አስባሪ | ተሳባሪ | አስተሳባሪ |
| ፈለጠ | ፈላጢ | ተፈላጢ | አፍላጢ | ተፋላጢ | አስተፋላጢ |
| ፀሐፈ | ፀሐፊ | ተፀሐፊ | አፅሐፊ | ተፃሓፊ | አስተፃሓፊ |

ተ
አ } አመልና ልማድ ይባላሉ።
አስተ

የ"ተ" ልማድ ***የመደረግና የመደራረግ*** ነው ተዘከረ፣ ተወክፈ፣ ባለ ጊዜ ግን ***የማድረግና የመደረግ*** አመል ይዞ ይገኛል የ"አ" ልማድ ***ማስደረግ*** ነው አንጦልዐ፣ አመረ፣ አንጸረ፣ ባለ ጊዜ ግን ***የመደረግና የማድረግ*** አመል ይዞ ይገኛል። የ"አስተ" ልማድ ***ማደራረግ*** ሲሆን አስተሐመመ፣ አስተቃሰመ፣ አስተበቍዐ፣ አስተብፅዐ፣ አስተጋብአ፣ ባለ ጊዜ ግን ***የመደረግ፣ የማድረግና የማስደረግ*** አመል ይዞ ይገኛል። በዚህም ምክንያት "አስተ" **ባለ ድርብ አመል** ተብሎ ይጠራል።

ሕጹፃን አዕማድ የሚባሉት የንባብ ገባሪ የትርጉም ተገባሪ ሲሆኑ በአደራደራቸውም አራት ወገን ናቸው።

ምሳሌ፦ ርሕበ - ተራብ ንግሠ - ነገሠ

ጸምአ - ተጠማ ክብረ - ከበረ

ሞተ - ሞተ ቆመ - ቆመ

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ግሶች በአምስቱ አዕማድ ሲረቡ የሚከተለውን ይመስላሉ።

| ግስ | ገባሪ | ተገባሪ | አግባሪ | ተጋባሪ | አስተጋባሪ |
|---|---|---|---|---|---|
| ንግሠ | ንግሠ | - | አንገሠ | ተናገሠ | አስተናገሠ |
| ክብረ | ክብረ | - | አክበረ | ተካበረ | አስተካበረ |
| ጸምአ | - | ጸምአ | አጽምአ | ተጻምአ | አስተጻምአ |
| ርሕበ | - | ርሕበ | አርሐበ | ተራሐበ | አስተራሐበ |

## ፫.፮. የአኃዝ ርባታ

የአኃዝ ርባታ ሦስት ደረጃዎች አሉት። እነሱም ነጠላ ቆጠራ፣ ርባታና ብዜታዊ ርባታ ናቸው።

**ሀ. ነጠላ ቆጠራ፡-**

| ትልቋዊ አኃዝ | ፊደላዊ አኃዝ |
|---|---|
| ፩ | አሐዱ |
| ፪ | ክልኤቱ |
| ፫ | ሠለስቱ |
| ፬ | አርባዕቱ |
| ፭ | ኀምስቱ |
| ፮ | ስድስቱ |
| ፯ | ሰብዓቱ |
| ፰ | ሰመንቱ |
| ፱ | ተሰዓቱ |
| ፲ | ዐሠርቱ |
| ፳ | ዕሥራ |
| ፴ | ሠላሳ |
| ፵ | አርብዓ |
| ፶ | ኀምሳ |
| ፷ | ስሳ |
| ፸ | ሰብዓ |
| ፹ | ሰማንያ |
| ፺ | ተስዓ |
| ፻ | ምዕት |

ሰ. ርብታ፡-

| ትልቋቀዊ አኃዝ | ፊደላዊ አኃዝ | ትርጓሜ |
|---|---|---|
| ፩ዱ ፩ዱ | አሐዱ አሐዱ | አንድ አንዱ አንደኛ አንደኛው |
| ፪ቱ ፪ቱ | ክልኤቱ ክልኤቱ | ኹለት ኹለቱ ኹለተኛ ኹለተኛው |
| ፫ቱ ፫ቱ | ሠለስቱ ሠለስቱ | ሦስት ሦስቱ ሦስተኛ ሦስተኛው |
| ፬ቱ ፬ቱ | አርባዕቱ አርባዕቱ | አራት አራቱ አራተኛ አራተኛው |
| ፭ቱ ፭ቱ | ኀምስቱ ኀመስቱ | አምስት አምስቱ አምስተኛ አምስተኛው |
| ፮ቱ ፮ቱ | ስድስቱ ስድስቱ | ስድስት ስድስቱ ስድስተኛ ስድስተኛው |
| ፯ቱ ፯ቱ | ሰብዓቱ ሰብዓቱ | ሰባት ሰባቱ ሰባተኛ ሰባኛው |
| ፰ቱ ፰ቱ | ሰመንቱ ሰመንቱ | ስምንት ስምንቱ ስምንተኛ ስምንተኛው |
| ፱ቱ ፱ቱ | ተሰዓቱ ተሰዓቱ | ዘጠኝ ዘጠኙ ዘጠነኛ ዘጠነኛው |
| ፲ቱ ፲ቱ | ዐሠርቱ ዐሠርቱ | ዐሥር ዐሥሩ ዐሥረኛ ዐሥረኛው |
| ፳ ፳ | ዕሥራ ዕሥራ | ኻያ ኻያው ኻያኛ ኻያኛው |
| ፴ ፴ | ሠላሳ ሠላሳ | ሠላሳ ሠላሳው ሠላሳኛ ሠላሳኛው |
| ፵ ፵ | አርብዓ አርብዓ | አርባ አርባው አርባኛ አርባኛው |
| ፶ ፶ | ኀምሳ ኀምሳ | አምሳ አምሳው አምሳኛ አምሳኛው |
| ፷ ፷ | ስሳ ስሳ | ስድሳ ስድሳው ስድሳኛ ስድሳኛው |
| ፸ ፸ | ሰብዓ ሰብዓ | ሰባ ሰባው ሰባኛ ሰባኛው |
| ፹ ፹ | ሰማንያ ሰማንያ | ሰማንያ ሰማንያው ሰማንያኛ ሰማንያኛው |
| ፺ ፺ | ተስዓ ተስዓ | ዘጠና ዘጠናው ዘጠናኛ ዘጠናኛው |
| ፻ ፻ | ምዕት ምዕት | መቶ መቶው መቶኛ መቶኛው |

ሐ. ብዜታዊ ርባታ፡-

| | ትልቋቀዊ አኃዝ | ትርጓሜ (በብዜት) | | ማስረጃ (ምስክር) |
|---|---|---|---|---|
| ፩ዱ | ፩ዱ ፩ዱ | አንድ ገዜ አንድ | አንድ | |
| | ፪ቱ ፪ቱ | ኹለት ጊዜ ኹለት | አራት | ፪ቱ ፪ቱ ኪሩቤል እለ ይጸውሩ መንበሮ ለልዑል እንዲል። |
| | ፪ቱ ፫ቱ | ኹለት ጊዜ ሦስት | ስድስት | ፪ቱ ፫ቱ ቃላተ ወንጌል አኮ ንሕነ ዘነዐቅቦሙ አላ እሙንቱ የዐቅቡነ ለድኂን ወለተጸውኖ እንዲል። |
| | ፪ቱ ፬ቱ | ኹለት ጊዜ አራት | ስምንት | ፪ቱ ፬ቱ ደቂቀ እሤይ። |
| | ፪ቱ ፭ቱ | ኹለት ጊዜ አምስት | ዐሥር | ፪ቱ ፭ቱ ቃላተ ኦሪት። |
| | ፪ቱ ፮ቱ | ኹለት ጊዜ ስድስት | ዐሥራ ኹለት | ፪ቱ ፮ቱ ሐዋርያት። |
| | ፪ቱ ፯ቱ | ኹለት ጊዜ ሰባት | ዐሥራ አራት | ፪ቱ ፯ቱ ቅዳሴያት። |
| | ፪ቱ ፰ቱ | ኹለት ጊዜ ስምንት | ዐሥራ ስድስት | ፪ቱ ፰ቱ ሕግጋት። |
| | ፪ቱ ፱ቱ | ኹለት ጊዜ ዘጠኝ | ዐሥራ ስምንት | |
| | ፪ቱ ፲ቱ | ኹለት ጊዜ ዐሥር | ኻያ | ፪ቱ ፲ቱ ዓለማት። |
| | ፪ቱ ፳ | ኹለት ጊዜ ኻያ | አርባ | |
| | ፪ቱ ፴ | ኹለት ጊዜ ሠላሳ | ስድሳ | |
| | ፪ቱ ፵ | ኹለት ጊዜ አርባ | ሰማንያ | |
| | ፪ቱ ፶ | ኹለት ጊዜ አምሳ | መቶ | |
| | ፪ቱ ፷ | ኹለት ጊዜ ስሳ | መቶ ኻያ | |
| | ፪ቱ ፸ | ኹለት ጊዜ ሰባ | መቶ አርባ | |
| | ፪ቱ ፹ | ኹለት ጊዜ ሰማንያ | መቶ ስድሳ | |
| | ፪ቱ ፺ | ኹለት ጊዜ ዘጠና | መቶ ሰማንያ | |
| | ፪ቱ ፻ | ኹለት ጊዜ መቶ | ኹለት መቶ | |
| | ፩ዱ ፩ዱ | አንድ ገዜ አንድ | አንድ | |
| | ፪ቱ ፪ቱ | ኹለት ጊዜ ኹለት | አራት | |
| | ፫ቱ ፫ቱ | ሦስት ጊዜ ሦስት | ዘጠኝ | ፫ቱ ፫ቱ ቅዱሳን በል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ፬ቱ ፬ቱ | አራት ጊዜ አራት | ዐሥራ ስድስት | ፪ቱ ፫ቱ ሕግጋት ያለውን ፬ቱ ፬ቱ ሕግጋት ቢልም ይሆናል። |
| | ፭ቱ ፭ቱ | አምስት ጊዜ አምስት | ኻያ አምስት | |
| | ፮ቱ ፮ቱ | ስድስት ጊዜ ስድስት | ሠላሳ ስድስት | ፮ቱ ፮ቱ ቅዱሳት አንስት በል። |
| | ፯ቱ ፯ቱ | ሰባት ጊዜ ሰባት | አርባ ዘጠኝ | |
| | ፰ቱ ፰ቱ | ስምንት ጊዜ ስምንት | ስሳ አራት | |
| | ፱ቱ ፱ቱ | ዘጠኝ ጊዜ ዘጠኝ | ሰማንያ አንድ | እም ፱ቱ ፱ቱ ቃላተ መጻሕፍት አልቦ ዘየሐጽጽ ወዘይትዌሰክ። ሲል ይገኛል። |
| ፪ቱ | ፲ቱ ፲ቱ | ዐሥር ጊዜ ዐሥር | መቶ | ፲ተ ፲ተ ኮነ ነገደ መላእክት እም ፲ቱ ፲ቱ ነገደ መላእክት ወድቀ አሐዱ ወተውህበ ለዕጓለእመ ሕያው ፺ወ፱ተ ነገደ ኮነ እንዲል። |
| | ፳ ፳ | ኻያ ጊዜ ኻያ | ኹለት መቶ | |
| | ፴ ፴ | ሠላሳ ጊዜ ሠላሳ | ዘጠኝ መቶ | |
| | ፵ ፵ | አርባ ጊዜ አርባ | ሺህ ስድስት መቶ | |
| | ፶ ፶ | አምሳ ጊዜ አምሳ | ኹለት ሺህ አምስት መቶ | |
| | ፷ ፷ | ስሳ ጊዜ ስሳ | ሦስት ሺህ ስድስት መቶ | |
| | ፸ ፸ | ሰባ ጊዜ ሰባ | አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ | |
| | ፹ ፹ | ሰማንያ ጊዜ ሰማንያ | ስድስት ሺህ አራት መቶ | |
| | ፺ ፺ | ዘጠና ጊዜ ዘጠና | ስምንት ሺህ አንድ መቶ | |
| | ፻ ፻ | መቶ ጊዜ መቶ | ዐሥር ሺህ (እልፍ) | |

# ምዕራፍ አራት
## ፬· አብዛኀያን
## ፬·፩ አብዛኀያን ፊደላት

አብዛኀያን ፊደላት የተባሉት ሰባት ናቸው። እነሱም ማን ማን ናቸው ቢሉ ለ፣ መ፣ ተ፣ ነ፣ አ፣ ወ፣ የ ናቸው።

ምሳሌ፦

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ለ ፡ ሲያበዛ | ኪሩብ | ያለውን | ኪሩቤል | ይላል |
| | | ሱራፊ | | ሱራፌል | |
| ፪ | መ ፡ ሲያበዛ | ኩሉ | ያለውን | ኩሎሙ | ይላል |
| | | አንተ | | አንትሙ | |
| ፫ | ተ ፡ ሲያበዛ | ካህን | ያለውን | ካህናት | ይላል |
| | | ሕጻን | | ሕጻናት | |
| ፬ | ነ ፡ ሲያበዛ | ጌር | ያለውን | ጌራን | ይላል |
| | | ቅዱስ | | ቅዱሳን | |
| ፭ | አ ፡ ሲያበዛ | ደብር | ያለውን | አድባር | ይላል |
| | | ወግር | | አውግር | |
| ፮ | ወ ፡ ሲያበዛ | አብ | ያለውን | አበው | ይላል |
| | | ሰሌዳ | | ሰላድው | |
| ፯ | የ ፡ ሲያበዛ | መርኤት | ያለውን | መራእይ | ይላል |
| | | መክሊት | | መካልይ | |
| | | ሌሊት | | ሊያልይ | |

## ፬·፪ የራብዕ ብዛት

ራብዕ አብዥዎች የተባሉት የሥሙን ድህረ መነሻ ራብዕ እያደረጉ የሚሄዱ ናቸው።

ምሳሌ፦ መቅደስ, መጥባህት, መዝራዕት } ያለውን — መቃድስ, መጣብህ, መዛርዕ } ይላል።

## ፬·፫ የካዕብ ብዛት

ካዕብ ባዛት ማለት በካዕብ ፊደል ወይም በሁለተኛ ፊደል ከነጠላ ወደ ብዙ የሚለወጥ ሥም ማለት ነው።

ምሳሌ፦ ወልድ ያለውን ውሉድ ይላል።

## ፬·፬ የብዙ ብዙ

ይህ ይብዛት ዓይነት በአንድ ሥም ላይ ሁለት አብዥ ፊደላት ሲገቡ የሚፈጠር ኢ ቀጥተኛ የብዛት ዓይነት ነው። ለምሳሌ፦

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | <u>የብዙ ብዙ</u> |
|---|---|---|
| ደብር | አድባር | አድባራት |
| እልፍ | አእላፍ | አእላፋት |
| ያፍ | አዕዋፍ | አዕዋፋት |
| ልብስ | አልባስ | አልባሳት |

## ፬.፭ ምልስ ብዛት

ይኽ የብዛት ዓይነት ደግሞ ነጠላ ቍጥሩ ብዙ ፣ ብዙ ቍጥሩ ደግሞ ነጠላ ቍጥር የሚመስልበት የብዛት ዓይነት ስለኾነ ምልስ ብዛት ተባለ። ለምሳሌ፦

| **ነጠላ** | **ብዙ** |
|---|---|
| መጥባሕት | መጣብሕ |
| መዝራዕት | መዛርዕ |
| አጽባዕት | አጻብዕ |
| ገራህት | ገራውህ |

## ፬.፮ የስም ብዛት

በአብዥ ፊደላት ሳይሆን በ"እለ" የሚበዙ ስሞችን ይያዘ የብዛት ዓይነት የሥም ብዛት ይባላል።

ለምሳሌ፦

| | | |
|---|---|---|
| እለ ጴጥሮስ | እነ ጴጥሮስ | የመሳሰለውን ይመለከቷል። |
| እለ ሙሴ | እነ ሙሴ | |
| እለ መኑ | እነ ማን | |

## ፬.፯ የሣልስ ቅጽል ብዛት

የሣልስ ቅጽል ብዛት ማለት ከግስ በሚወጡ ሳልስ ቀጽሎች ላይ የሚታይ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ሲሆን የወንዶች በ"ያን" ሲበዛ የሴቶች ደግሞ በ"ያት" ይበዛል።

ምሳሌ፦

| ግስ | የተባዕታይ ሣልስ | ቅጽል ብዛት | የአንስታይ ሣልስ | ቅጽል ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | ቀታሊ | ቃታሊያን | ቀታሊት | ቀታሊያት |
| ቀደሰ | ቀዳሲ | ቀዳሲያን | ቀዳሲት | ቀዳሲያት |
| ተንበለ | ተንባሊ | ተንባሊያን | ተንባሊት | ተንባሊያት |
| ባረከ | ባራኪ | ባራኪያን | ባራኪት | ባራኪያት |
| ማሕረከ | ማሕራኪ | ማሕራኪያን | ማሕራኪት | ማሕራኪያት |
| ሴሰየ | ሴሳዪ | ሴሳዪያን | ሴሳዪት | ሴሳዪያት |
| ክህለ | ክሃሊ | ክሃሊያን | ክሃሊት | ክሃሊያት |
| ጦመረ | ጦማሪ | ጦማሪያን | ጦማሪት | ጦማሪያት |

## ፬.፰. ሳድስ ቅጽል ብዛት

የሳድስ ቅጽል ብዛት ማለት ከግስ በሚወጡ ሳድስ ቀጽሎች ላይ የሚታይ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ሲሆን የወንዶች በ"ን" ሲበዛ የሴቶች ደግሞ በ"ት" ይበዛል፡፡

ምሳሌ፡-

| ግስ | ተባዕታይ ሳድስ | ቅጽል ብዛት | አንስታይ ሳድስ | ቅጽል ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | ቅቱል | ቅቱላን | ቅትልት | ቅቱላት |
| ቀደሰ | ቅዱስ | ቅዱሳን | ቅድስት | ቅድሳት |
| ተንበለ | ትንቡል | ትንቡላን | ትንብልት | ትንቡላት |
| ባረከ | ብሩክ | ቡሩካን | ቡርክት | ቡሩካት |
| ማሕረከ | ምሕሩክ | ምሕሩካን | ምሕርክት | ምሕሩካት |
| ሴሰየ | ሲሱይ | ሲሱያን | ሲስይት | ሲሱያት |
| ክህለ | ክሁል | ክሁላን | ክህልት | ክሁላት |
| ጦመረ | ጡሙር | ጡሙራን | ጡምርት | ጡሙራት |

## ፬.፱ የባዕድ ቅጽል ብዛት፡

የባዕድ ቅጽል ብዛት ማለት ከግስ በሚወጡ ባዕድ ቀጽሎች ላይ የሚታይ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ሲሆን የወንዶች በ"ን" ሲበዛ የሴቶች ደግሞ በ"ት" ይበዛል፡፡

ምሳሌ፦

| ግስ | ተባዕታይ ባዕድ | ቅጽል ብዛት | አንስታይ ባዕድ | ቅጽል ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | መቅትል | መቅትላን | መቅትልት | መቅትላት |
| | መስተቅትል | መስተቅትላን | መስተቅትልት | መስተቅትላት |
| | መስተቃትል | መስተቃትላን | መስተቃትልት | መስተቃትላት |
| ቀደሰ | መቀድስ | መቀድሳን | መቀድስት | መቀድሳት |
| | መስተቀድስ | መስተቀድሳን | መስተቀድስት | መስተቀድሳት |
| | መስተቃድስ | መስተቃድሳን | መስተቃድስት | መስተቃድሳት |

## ፬.፲ የማይበዙ ሥሞች

በየትኛውም ቋንቋ ስዋስዋዊ መርህ መሰረት እነዚህ ሥሞች የማይበዙ በነጠላነታቸው ፀንተው ሲታወቁ የሚኖሩ ሥሞች ናቸው እነሱም ሃይማኖት ፣ ፀሐይ ፣ ወርሕ የመሳሰሉት ሲሆኑ <u>***ጉልት***</u> ተብለው ይጠራሉ፡፡

## ፬.፲፩ ነጠላም ብዙም ሥሞች

እነዚህ ሥሞች በተለየ ሁኔታ ለነጠላ ቊጥር ለብዙ ቊጥር እየቻሉ የሚረቡ የሥም ዓይነቶች ናቸው፡፡

ምሳሌ፦

| ነጠላ | ብዛት | በአንድ በብዙ |
|---|---|---|
| እግር | አእጋር | እገር |
| ዕብን | አዕባን | ዕበን |
| ዕፅ | ዕፅዋት | ዕፀው |
| እስራኤል | እስራኤል | እስራኤል |
| ሕዝብ | አሕዛብ | ሕዘብ |
| ፀር | አፅራር | ፀር |
| ሐራ | ሐራ | ሐራ |
| ቢፅ | አብያፅ | ቢፅ |

# ምዕራፍ አምስት

## ፭. አገባባት

አገባብ የሚባለው በሰዋስዋዊ መዋቅር ውስጥ እየገባ ያልተስማሙ ዐረፍተ ነገሮችን የሚያስማማ ሲሆን እንደሌሎቹ የሰዋስው ክፍሎች ግን ራሱን ችሎ የመቆምና ብቻውን ትርጉም የመስጠት ልማድ የለውም።

አገባባት በሦስት ይከፈላሉ እነሱም

| | |
|---|---|
| ዐቢይ አገባብ<br>ደቂቅ አገባብ<br>ንዑስ አገባብ | ይባላሉ |

## ፭.፩ ዐቢይ አገባብ

ዐቢይ አገባብ የተባለበት ምክንያት በዐረፍተ ነገር ውስጥ በዐበይት አናቅጽ ላይ እየወደቀ ዐበይት አናቅጹን ከማሰሪያነት ስለሚያስቀራቸው ነው።

ምሳሌ፡- አዳም ተኰነነ እስመ/አምጣነ/አኮኑ በልዐ በለሰ።

ክርስቶስ ውእቱ ዘገብረ ሠላመ።

እንተ ትገብሩ ፅድቀ ኢትፍርሑ ሞተ።

እለ ሰበኩ ወንጌለ ክርስቶስ ሐዋርያት ውእቶሙ።

በዝንቱ ትዕምርተ መስቀል ሐዋርያቲሁ ለዘሞተ እንዘ ይግብሩ ተዓምራተ ሰደዱ አጋንንተ ወሰበሩ ጣዖታተ።

ከምሳሌው ማየት እንደተቻለው ዐበይት አገባባት የተባሉት፡-

| | |
|---|---|
| እስመ<br>አኮኑ<br>ዘ<br>አምጣነ<br>እለ<br>እንተ<br>እንዘ | ናቸው። |

## ፭.፪. ደቂቅ አገባብ

ይህ አገባብ ደቂቅ አገባብ የተባለበት ምክንያት እንደ ዐቢይ አገባብ በዐበይት አናቅጽ ላይ እየወደቀ ዐበይት አናቅጽን ከማሰሪያ አንቀጽነታቸው የሚያስቀር ሳይሆን በሥም ላይ ብቻ እየወደቀ ያልተስማሙ ዐረፍተ ነገሮችን ስለሚያስማማ ነው።

**ምሳሌ**፡-እህትየ ሆረት ኀበ ቤተ ከኒሳ።

- እስራኤል ሰገዱ ለአምላከ እዝራ።
- ኤርምያስ ወሕዝበ እስራኤል ተማሕረኩ በንጉሠ ባቢሎን።
- ዝንቱ ውእቱ ብእሲ ይመስል ከመ አንበሳ።

- ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሞተ **ህየንተ** ሃይማኖቱ፡፡
- አኮ መላእክተ እግዚአብሔር ወአኮ ተንባሊያን አላ ለሊሁ እግዚእ መጽዐ ወደምሰሰ አበሳነ ተሰቂሎ በማዕከለ ምድር፡፡
- አልቦ ነገረ ሐዲስ **እም** ታሕተ ሰማይ፡፡

ከላይ በምሳሌው እንደተገለፀው በስሞች ላይ ወድቀው ያልተስማሙ ዐረፍተ ነገሮችን የሚያስማሙ ደቂቅ አገባባት የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ኀበ | ላይ |
| ለ | በቁሙ |
| በ | በቁሙ |
| ከመ | እንደ |
| ህየንተ | ስለ |
| መንገለ | ወደ |
| ላዕለ | ላይ |
| ታህተ | ታች |
| ማዕከለ | መካከል |
| ውስተ | ውስጥ |
| እም | ከ |

## ፯.፫. ንዑስ አገባብ

ይህ አገባብ ንዑስ አገባብ የተባለበት ዋና ምክንያት እንደ ዐቢይ አገባብ በዐበይት አናቅጽ ላይ እንደ ደቂቅ አገባብ በሥም ላይ የሚወድቅ ሳይሆን በቅጽልነትና በግስ ገላጭነት እየገባ የሚያገለግል ስለሆነ ነው፡፡

ምሳሌ፡- **ምንት** ነገር ተገብረ ብነ
**አይ** ልሳን ዘይክል ነቢበ ዘይትነገር በእንቲአኪ
ክርስቶስ **ማዕዜ** ተወልደ
**አይቴ** ሖረ
**ናሁ** ሰማዕናሁ በኤፍራታ
**ዮም** ተወልደ ህፃን በቤተልሔም
**ጌሰም** ንሐውር ኀበ ቤተ ከኒሳ
**እፎ** መጻዕከ ዝየ ውስተ ፅልመት
ክርስቶስ **እንቋዕ** ቀተለብነ ጸላዒነ
**በእንተ** ዲያብሎስ መሐረነ ክርስቶስ

ከላይ በምሳሌው እንደተገለፀው ንዑስ አገባባት የሚባሉት በሚከተለው ሠንጠርዥ ላይ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምንት | ምን | አሌ | ወዮ |
| አይ | ምን | ነየ | እነሆ |
| ናሁ | አሁን | ነያ | እነኋት |
| ዮም | ዛሬ | | |
| እንቋዕ | እንኳን፣ እሰይ ውጭኝ ውጭኝ | | |
| ክመ | መቼም መች | | |
| ነየ | እነሆ | | |
| እንተ | ደስ አይበለው ብለህ (ስትል) | | |
| ማዕዜ | መቼ | | |
| አይቴ | የት | | |
| ጌሰም | ነገ | | |
| እፎ | እንዴት በእንዴት | | |

# ምዕራፍ ስድስት
## ፮. ገቢር ተገብሮ
### ፮.፩. ገቢር

ገቢር ማለት በተሻጋሪ ወይም በገቢር ግሶች አማካኝነት በምንተረጉምበት ጊዜ በመድረሻው "ን" የሚል ፍች የሚያመጣ ማለት ነው። በዝርዝር ሐሳብ ግልጽ ሆኖ ሲብራራ በሚከተለው ሁኔታ ይገለጻል።

ሳድስ ወደ ግእዝ<br>
ካዕብ ወደ ሳብዕ } ይለወጣሉ<br>
ሣልስ ወደ ሐምስ

ምሳሌ፡- ቤት ፡ ቤተ<br>
ክብር ፡ ክብረ<br>
ገጹ ፡ ገጸ<br>
ልብሱ ፡ ልብሶ<br>
ብእሲ ፡ ብእሴ<br>
ዘማሪ ፡ ዘማሬ

ዐረፍተ ነገሮች፡- ሰሎሞን ሐነጸ ቤተ።<br>
ኤልያስ ኀሰሰ ክብረ።<br>
አይሁድ ጸፍዕዎ ለክርስቶስ ገጸ።<br>
ውእቱ ሰጠጠ ልብሶ።<br>
ክርስቶስ አፍቀረ ብዕሴ።<br>
ያሬድ ዘመረ ዝማሬ።

### ፮.፪. ተገብሮ

ተገብሮ ማለት በተሻጋሪ ወይም በተገብሮ ግሶች አማካኝነት በምንተረጉምበት ጊዜ "ምን" የሚል ጥያቄ ሳያነሳ ባለቤት ወይም ድርጊት ፈጻሚ እየሆነ የሚያገለግል ማለት ነው።

በዚህም ጊዜ፡- ግእዝ ወደ ሳድስ<br>
ሳብዕ ወደ ካዕብ } ይለወጣሉ<br>
ሐምስ ወደ ሣልስ

ምሳሌ፡- ልብሰ ፡ ልብስ<br>
ማሕደረ ፡ ማሕደር<br>
ቅዱሶ ፡ ቅዱሱ<br>
ቀታሌ ፡ ቀታሊ

ዐረፍተ ነገሮች፡- ልብስ ተአንመ።<br>
ተሐነፀ ማሕደር።<br>
ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ተንስአ።<br>
ቀታሊ ሰብእ ኢይትፈቀር በኀበ ሰብእ።

በራብዕ የሚያልቁ ስሞች ግን ለገቢርም ለተገብሮም ይችላል።

ምሳሌ፡- ደብተራ<br>
መና<br>
ደመና

ዐረፍተ ነገሮች፡-

| | |
|---|---|
| አብርሃም ተከለ ደብተራ:: | ገቢር |
| ተተክለ ደብተራ:: | ተገብሮ |
| ሙሴ አውረደ መና:: | ገቢር |
| መና ወረደ:: | ተገብሮ |
| ሚካኤል ጸለለ ደመና ለሕዝበ እስራኤል:: | ገቢር |
| ደመና ተርዕየ በሰማይ:: | ተገብሮ |

## ፮.፫ አሥማት

የሥም ዓይነቶች አራት ናቸው እነሱም

፩. የባሕርይ ሥም ⟹ አምላክ፣ ሰው
፪. የተጸውኦ ሥም ⟹ አዳም
፫. የተቀብኦ ሥም ⟹ ገብረ ሥላሴ፣ መድኃኔዓለም
፬. የግብር ሥም ⟹ መምህር፣ ዶክተር

ዘርፍ የያዘ የተቀብዖ ሥም ለገቢር ለተገብሮ ይከታል:: ለዚሁም መዕቀበ አልፋን፣ ተክለ ሃይማኖትን፣ ገብረ መንፈስ ቅዱስን፣ መድኃኔ ዓለምን የመሳሰለውን አዋጅ ይመለከቷል:: የተጸውዖ ሥም ግን በገቢር ጊዜ "ሀ" ይጨምራል:: ለዚሁም ማስረጃ *"ፈነወ ሙሴሀ ገብሮ ወአሮንሀ ኀሩዮ"* ሲል ይገኛል:: የሀገር ሥሞች ፍጹም ሳድስ ከሆኑት ግብፅን፣ ጽርዕን፣ ሕንድን፣ ምስርን ከመሳሰሉት በስተቀር ለገቢርም ለተገብሮም ይችላሉ:: ይኼውም ይታወቅ ዘንድ "ዐርገ ኢየሩሳሌም ወዐደወ ዮርዳኖስ" የሚል አዋጅ ይገኛል:: ነገር ግን በልዩ ሁኔታ "ንግደትኪ ማርያም ቁስቋመ እምሎዛ ለምእመናንኪ ይኩነነ ቤዛ" ባለ ጊዜ "ዐርገ ኢየሩሳሌም ወዐደወ ዮርዳኖስ" የሚለውን አዋጅ ያፈርሰዋል:: ፍጹም ሳድስ የሆኑት የሀገር ሥሞች ግን ገቢር ለማድረግ ወደ ግእዝ ይቀየራሉ::

ይህም፡-

| | | |
|---|---|---|
| ግብጽ | ግብጸ | |
| ጽርዕ | ጽርዐ | ወደሚል ይቀየራሉ |
| ሕንድ | ሕንደ | |
| ምስር | ምስረ | |

# ምዕራፍ ሰባት

## ፯. ዘርፈ ሰዋስው

ዘርፈ ሰዋስው ማለት የሰዋስው ውበት ሁለት ቃላት በአንድ ሐረግ ተናበው አንድ ጥምር ቃል ወደ መሆን የሚቀየሩበት ክፍለ ሰዋስው ነው:: ሁለት ግእዛውያት ቃላት በሚናበቡበት ጊዜ የሚመሰረተው አንድ ቃል ባለቤትና ዘርፍን የያዘ ሲሆን መነሻው የግእዝ ቃል ባለቤት መድረሻው የግእዝ ቃል ደግሞ ዘርፍ ይባላል::
ለምሳሌ፡- ዐምደ ሃይማት፣ ምሥጢረ ሥላሴ የሚሉት በዘርፈ ሰዋስው የተመሠረቱ ቃላት *"ዐምድ"* እና *"ምሥጢር"* ባለቤት ሲሆኑ፤ *"ሃይማኖት"* እና *"ሥላሴ"* ደግሞ ዘርፍ ይባላሉ ማለት ነው::
በሌላ አገላፅ በዘርፈ ሰዋስው የሚመሰረቱ ቃላት ዘርፍ ያዥና ዘርፍ የሚባሉ ሲሆን ዘርፍ ያዥ ምንጊዜም በቃሉ መነሻ ዘርፍ ደግሞ ምንጊዜም በቃሉ መድረሻ ይገኛሉ::
ምሳሌ፡- ቤተ እስራኤል፣ ሀገረ እግዚአብሔር፣ መጋቤ ሐዲስ፣ ተስፋ አበው፣ ዜና ቅዱሳን፣ ተዓምረ ማርያም የሚሉትን ቃላት ስናይ ዘርፍ ያዥ ቤት፣ ሀገር፣ መጋቢ፣ ተስፋ፣ ዜና እና ተዓምር የሚሉት ሲሆኑ፤ እስራኤል፣ እግዚአብሔር፣ ሐዲስ፣ አበው፣ ቅዱሳንና ማርያም የሚሉት ደግሞ ዘርፍ ናቸው::
ዘርፈ ሰዋስው በሚተረጎምበት ጊዜም የቃሉ መነሻ ባለቤት እንደሆነ ሲቀጥል በመድረሻ ያለው ቃል "የ" የሚል ቀዳማይ ቅጥያ እያስቀደመ ዘርፍ ሆኖ ይተረጎማል::

ምሳሌ፡- ፍኖተ ጽድቅ፡ የጽድቅ መንገድ
አካለ ክርስቶስ፡ የክርስቶ አካል
አዕማደ ምሥጢር፡ የምሥጢር ምሰሶዎች
መርጡለ ማርያም፡ የማርያም አዳራሽ
ነገረ መለኮት፡ የመለኮት ነገር

በዘርፈ ሰዋስው ሕግ መሠረት የግእዝ ቃላት በሁለት ይከፈላሉ እነሱም ተናባቢያንና ኢተናባቢያን ቃላተ ግእዝ ይባላሉ፡፡

### ፫.፩. ተናባቢያን ቃላተ ግእዝ

በዘርፈ ሰዋስው ምሥረታ ጊዜ የዘርፍ ያገቹ ወይም የመነሻው ቃል መድረሻ ቀለም ሳድስ ቢሆን ወደ ግእዝ፣ ሣልስ ቢሆን ወደ ኃምስ ተቀይሮ፤ ራብዕ፣ ኃምስና ሳብዕ ሳይቀየሩ ከዘርፉ ጋር ተናበው ዘርፈ ሰዋስው ይመሠረታል፡፡

ምሳሌ፡- በሳድስ፡ ልሳነ ግእዝ
በሣልስ፡ ፈጣሬ ዓለማት
በራብዕ፡ ደመና ኤልያስ
በኃምስ፡ ውዳሴ ማርያም
በሳብዕ፡ መሰንቆ ዳዊት

በዘርፈ ሰዋስው ሕግ መሠረት በተናባቢያን ቃላተ ግእዝ ዘርፈ ሰዋስው ምሥረታ ጊዜ፡-

ነጠላ ከነጠላ
ነጠላ ከብዙ
ብዙ ከብዙ
ብዙ ከነጠላ
} እየተናበበ ይመሠረታል፡፡

ምሳሌ፡- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከነጠላ ግእዛዊ ቃል ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-
ንጉሠ ሰማይ
ቤተ መንግሥት
ኃይለ ልዑል

- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-
  አምላከ አማልክት
  ቤተ አሕዛብ
  ክብረ ነገሥት
- ብዙ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-
  አዕማደ ምሥጢራት
  አብያተ ክርስቲያናት
  ነገሥተ ዓለማት
- ብዙ ግእዛዊ ቃል ከነጠላ ግእዛዊ ቃል ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-
  ከዋክብተ ሰማይ
  መጻሕፍተ ብሉይ
  ቃላተ ወንጌል

### ፫.፪. ኢተናባቢያን ቃላተ ግእዝ

ኢተናባቢያን ቃላተ ግእዝ የሚባሉት የዘርፈ ሰዋስው መነሻ ወይም ባለቤት ሆነው የሚያገለግሉ ቃላተ ግእዝ መድረረሻ ቀለማቸው ካዕብ፣ ሣልስና ሳድስ የሆኑ ሲሆኑ መነሻው ግእዛዊ ቃል ከመድረሻው ግእዛዊ ቃል ጋር ስለማይናበብ ዘ፣ ለ፣ እለ፣ እንተ በዘርፍ አያያዥነትም በዘርፍ ደፊነትም ቢሉ እየገቡ በማናበብ ዘርፈ ሰዋስው እንዲመሠረት ደርጋሉ፡፡ የእነዚህንም ዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

"ዘ"
ነጠላን ከነጠላ
ነጠላን ከብዙ
ብዙን ከብዙ
ብዙን ከነጠላ
} እያናበበ ዘርፈ ሰዋስው ያስመሠርታል፡፡

ምሳሌ፡- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከነጠላ ግእዛዊ ቃል በ"ዘ" ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-
በካዕብ፡ ብርሃኑ ዘፀሐይ
በሣልስ፡ ፀላዒ ዘቅዱስ

በሳድስ፡ ኃይል ዘአንበሳ

- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል በ“ዘ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-

  ቀታሊ ዘፀላእያን
  ቃል ዘአበው
  ኪዳን ዘቅዱሳን

- ብዙ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል በ“ዘ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-

  ምሥጢራት ዘሰማያት
  ሕጻናት ዘዓለማት
  ግብራት ዘሐዋርያት

- ብዙ ግእዛዊ ቃል ከነጠላ ግእዛዊ ቃል በ“ዘ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠረት፡-

  መላእክት ዘሰማይ
  ካህናት ዘደብር
  ወንጌላት ዘክርስቶስ

“ለ”

ነጠላን ከነጠላ
ብዙን ከብዙ
ነጠላን ከብዙ
} እያናበበ ዘርፈ ሰዋስው ያስመሠርታል፡፡

ምሳሌ፡- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከነጠላ ግእዛዊ ቃል በ“ለ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠርት፡-

  ብሔሩ ለነቢይ
  ጥበቡ ለንጉሥ
  ሥልጣኑ ለጳጳስ

- ብዙ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል በ“ለ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠርት፡-

  መዛግብቲሆሙ ለሰማያት
  ምግባራቲሆሙ ለኃጥአን
  መናብርቲሆሙ ለነገሥታት

- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል በ“ለ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠርት፡-

  መምህሮሙ ለአርድዕት
  ሠረገላሆሙ ለቅዱሳን
  ስብከቶሙ ለሐዋርያት

“እንተ”

ነጠላን ከነጠላ
ነጠላን ከብዙ
} እያናበበ ዘርፈ ሰዋስው ያስመሠርታል፡፡

ምሳሌ፡- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከነጠላ ግእዛዊ ቃል በ“እንተ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠርት፡-

  ማኅሌት እንተ ያሬድ
  ልብስ እንተ መርዓዊ
  ገብር እንተ ንግሥ

- ነጠላ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል በ“እንተ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠርት፡-

  ፍኖት እንተ ቅዱሳን
  ክንፍ እንተ መላእክት
  መልአክ እንተ አድባራት

“እለ”

ብዙን ከብዙ
ብዙን ከነጠላ
} እያናበበ ዘርፈ ሰዋስው ያስመሠርታል፡፡

ምሳሌ፡- ብዙ ግእዛዊ ቃል ከብዙ ግእዛዊ ቃል በ“እንተ” ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠርት፡-

  መነኰሳት እለ ገዳማት
  ብርሃናት እለ ከዋክብት
  ዓሣት እለ ማያት

➢ ብዙ ግእዛዊ ቃል ከነጠላ ግእዛዊ ቃል በ"እንተ" ተናቦ ዘርፈ ሰዋስው ሲመሠርት፦

አጽራር እለ ሰብእ
አዕማድ እለ ቤት
መራኅያን እለ ሀገር

እስከዚህ በዘርፈ ሰዋስው ያየነው የ"ዘ"፣ የ"ለ"፣ የ"እንተ"፣ እና የ"እለ" አጠቃቀም በዘርፍ አያያዥነት ሲሆን፤ ዘእግዚአብሔር ቃል፣ እንተ ኤልያስ ትንቢት፣ እለ ቅዱሳን ሕይወት፣ ለአብርሃም ክብሩ ባለ ጊዜ ግን የ"ዘ"፣ የ"እንተ"፣ የ"እለ" እና የ"ለ" አጠቃቀም በዘርፍ ደፊነት መሆኑን አስተውል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

## ፰. ሥርዓተ ንባብ

ሥርዓተ ንባብ ማለት የንባብ ሕግና ደንብ ወይም ስልተ ንባብ ማለት ሲሆን የንባብ ዓይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነሱም፦

ተነሽ
ተጣይ
ሰያፍ
ወዳቂ
} ናቸው፡፡

### ፰.፩. ተነሽ ንባብ

ይህ የንባብ ዓይነት የቃሉን መድረሻ ቀለም ከፍ አድርጎ በማንሳት በኃያል ድምጽ የሚነበብ ሲሆን ከሰባቱ ቀለማት በአምስቱ ማለትም በግእዝ፣ በካዕብ፣ በሣልስ፣ በራብዕ እና በሳብዕ ይገራል፡፡

ምሳሌ፦ ፩. በግእዝ፦

ቀተለ
አንተ
ንሕነ
አነ
ሠርዐ
ክመ

የመሳሰሉት ሲሆኑ ከይቤ በስተቀር ሁሉም ግሶች በግእዝ ቀለም ስለሚጨረሱ በኃያል ድምጽ የሚነበቡ ተነሽ ቀለማት ናቸው፡፡

፪. በካዕብ፦

አእመሩ
ውእቱ
ውእቶሙ
አንትሙ
መሀሩ
ሖሩ

፫. በሣልስ፦

አንቲ
ይእቲ
ኀቤኪ
ምስሌኪ
እንግድዓኪ
ንዒ
ቅትሊ
ሑሪ

፬. በራብዕ፡-

ተራክባ (አንስት ሣልሳይ መደብ)

አእመራ » » »

ቀድሳ (ትእዛዛዊ ግስ)

፮. በሳብዕ፡-

ሀቦ
ቅትሎ
አእምሮ
ቀድሶ
ተዘከሮ

(ሀቦ፣ ቅትሎ፣ አእምሮ፣ ቀድሶ፣ ተዘከሮ) ሁሉም ትእዛዛውያን ግሶች ናቸው፡፡

### ፳.፪. ተጣይ ንባብ

ተጣይ ንባብ ማለት ዝቅ ባለ በንዑስ ድምጽ የሚነበብ፤ ስልተ ንባቡም የቃላትን መድረሻ ቀለም አጠር ዋጥ ላላ በማድረግ የነበብ ሲሆን በሳድስ ብቻ ይነገራል፡፡ ምሳሌ፡- ይክል፣ ርግብ፣ ኃይል፣ ሰማይ፣ ጊዮርጊስ፣ ካህናት የመሳሰለው ሁሉ ነው፡፡

### ፳.፫. ሰያፍ ንባብ

ይህ የንባብ ዓይነት ተሰየፎ እንደ ተነሽ በኃያል ድምጽ የሚነበብ ሲሆን ስልተ ንባቡም የቃላት ቅድመ መድረሻ ቀለማት ረገጥ ያዝ ጎላ ገዘፍ ከፍ በማድረግ መድረሻ ቀለሙን ዋጥ በማድረግ በማሳጠር በማላላት ይነበባል፡፡ ሰይፍ ንባብ እንደ ተጣይ ንባብ በሳድስ ብቻ ይነገራል፡፡ ሰያፍ ንባብ በአንቀጽም መሥምም ይነገራል፡፡

ምሳሌ፡- አንቀጽ፡- ይገብር፣ ይቄድስ፣ የአምር የመሰለው ሁሉ ነው፡፡ በሥም፡- አማኑኤል፣ ኢሳይያስ፣ አብርሃም፣ ጳውሎስ፣ ጽዮን የመሰለው ሁሉ ነው፡፡

### ፳.፬. ወዳቂ ንባብ

ወዳቂ ንባብ እንደ ተጣይ ንባብ በንዑስ ድምጽ የሚነበብ ሲሆን የቃሉ መድረሻ ቀለም ረዘምና ጎተት ተደርጎ በመጣል የሚነበብ ስልት አለው፡፡ ተጣይ ንባብ እስካሁን ካየናቸው የንባብ ዓይነቶች ተለይቶ በ፯ቱ ቀለማት ይነገራል፡፡

ምሳሌ፡- ፩. በግእዝ፡-

አሐደ
ክልኤተ
አስመ
አምጣነ
መንገለ

፪. በካዕብ፡-

ሠለስቱ
አርባዕቱ
እረገሪሁ
ከበሮሁ

፫. በሣልስ፡-

አሐቲ
ዛቲ
ቀታሊ
ቀዳሲ
በእሲ
ጠሊ
ደመና

፬. በራብዕ፡-

መና
ሶልያና
ሙስና
ትጎትና
ደመና

፭. በኃምስ፡-

ቅዳሴ

ሥላሴ

ራምሴ

ምናሴ

ሙሴ

፮. በሳድስ፡-

ዝ ብቻ

፯. በሳብዕ፡-

ከበሮ

መሰንቆ

ደማስቆ

አኮ

## ፰.፭. ተቈጣሪና ተጠቅላይ ንባብ

**ሀ. ተቆጣሪ ንባብ፡-** ይህ የንባብ ዓይነት በሥርዓተ ንባብ ውስጥ የሚካተት ሆኖ ስልተ ንባቡን ስንመለከትም በአንድ ግእዛዊ ቃል ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ቀለማት ተቆጥረው የሚነበቡበት ሥርዓተ ንባብ ነው፡፡ ቃላቱ ግን በአራቱም ንባባት ሊነገሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተቆጥረው የሚነበቡ ቃላት ባለሙሉ ቀለም ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ከተነሽ፡ ዜነወ፣ ሌለየ፣ ሰዐለ
ከተጣይ፡ ማርያም፣ ገዳም፣ ቅዱሳን
ከሰያፍ፡ አማኑኤል፣ ጳውሎስ፣ ይገብር
ከወዳቂ፡ ሠረገላ፣ ከዋላ፣ ጰጥርቃ የመሳሰሉት ሁሉ ተቆጠረው ስለሚነበቡ ተቆጣሪ ይባላሉ፡፡

**ለ. ተጠቅላይ ንባብ፡-** ይህ ንባብም እንዲሁ በሥርዓተ ንባብ ውስጥ የሚካተት ሲሆን በአነባብ ስልቱ ግን ከተቆጣሪ ንባብ በተቃራኒ በግእዛዊ ቃሉ መሀል ላይ የሚገኙ ሳድስ ቀለማት ተጠቅልለው የሚነበቡበት ስልተ ንባብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ርግብ፣ እንተ፣ በኵር፣ ይክል፣ እስትንፋስ፣ አንሶሰወ፣ አስተቃተለ የመሳሰሉትን ሁሉ የያዘ ሲሆን ከርግብ ግ፣ ከአንተ ን፣ ከበኵር ኵ፣ ከይክል ክ፣ ከእስትንፋስ ን፣ ከአስተቃተለ ስ በጉሮሮ ድምጽ ተውጠው ባለ ሦስቱ ባለ ሁለት፣ ባለ አምስቱ ባለ አራት፣ ባለ ሰባቱ ባለ ስድስት ቀለም (ፊደል) እንዲሆን በመድረጋቸው በሊቃውንት ቋንቋ ወሃጥያን ንባባት ተበለው ይጠራሉ፡፡

**ሐ. ተቆጣሪም ተጠቅላይም፡-** በዚህ የአነባበብ መርህ መሠረት በግእዝ ቃላት ውስጥ የሚገኝ አንድ ቀለም ሁለቱንም ሚና የሚጫወት ማለትም ተቆጥሮም ተጠቅሎም መነበብ የሚችል ከሆነ ተቆጣሪና ተጠቅላይ ንባብ ይባላል፡፡ እንዲህ ዓይነት አመል ያላቸው ቀለማት ደግሙ ህ እና እ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ፩. በ"ህ" ክህለ፣ ብህለ የሚሉት ግሶች ይክህል ይብህል ይላል የኼውም ሲቆጥር ነው፡፡ ሲጠቀልል ግን ይክል፣ ይብል ይላል፡፡ በክህለ ቤት የሚገኙ ግሶች እንዲህ ዓይነት አመል እንዳላቸው አስተውል፡፡

፪. በ"እ" ሲቆጠር አእመረ፣ አዕረፈ የሚለው ሲጠቀለል አይመረ፣ አይረፈ በሚል ዘይቤ "እ"ን በ"ይ" ጠቅልሎ ይናገሯል፡፡

## ፰.፮. የሚጠብቁና የሚላሉ ምንባባት

ይህ የንባብ ሕግ በግእዝ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ቋንቋዎች የተለመደ ሲሆን የሚጠብቀውን አላልቶ የሚላላውን አጥብቆ ማንበብ የቋንቋ ዕውቀት ሕፀፅ ከመሆኑም በላይ ምሥጢርና ትርጉም የሚያበላሽ በመሆኑ አቅልሎ በማየት አይገባም፡፡

ምሳሌ፡- ፩. ወደሰ፣ ይገብር፣ አእምሮ፣ ክመ የሚሉት ቃላት ጠበቀው የሚነበቡ ቃላት ሲሆኑ ወደሰ ካለው ደ ይገብር ካለው ብ አእምሮ ካለው ሮ ክመ ካለው መ ጠብቀው ይነገራሉ፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው ጠብቀው የሚነገሩ ቀለማት ከቃሉ መካከል እና በቃሉ መጨረሻ ብቻ እንጂ በመነሻ እንደማይገኙ ልብ ይሏል፡፡

፪. መሰለ፣ ይቀትል፣ ጴጥሮስ፣ ወልድ የመሳሰሉት ቃላት ደግሞ ሁሉም ፊደላቸው ሳልተው የሚነበቡ በመሆናቸው ልኁሉኃን ቀለማት ምንባባት ይባላሉ፡፡

### ፰.፮. ዘላቂና ኀራጅ የንባብ ዓይነቶች

ይህ ሥርዓተ ንባብ ሦስት ባሕሎች አሉት፡፡ እነዚህም ፩. ኀራጅም ዘላቂም፣ ፪. የሚኀረድ እንጅ የማይዘልቅ፣ ፫. የሚዘልቅ እንጅ የማይኀርድ ይባላሉ አንድ ግእዛዊ ቃል በምልዓትም አጥሮም በሁለት ሥርዓተ ንባብ የሚነበብ ከሆነ ዘላቂና ኀራጅ ንባብ ይባላል፡፡ አጥሮ የሚነበብ ከሆነ ይኀረዳል እንጅ አይዘልቅም የሚባል ሲሆን፤ በምልዓት ዘልቆ የሚነበብ ከሆነ ደግሞ ይዘልቃል እንጅ አይኀርድም ይባላል፡፡ በዚህ ጽሑፍ ገጽ ፲፩ የግስ አዋጅ በሚለው ንዑስ ርዕስ አንቀጽ ፲፣ ፲፪ እና ፲፫ ላይ የተጠቀሰውን ለዚህ ምሳሌ እናመጣለን፡፡

ምሳሌ፡- ፩. ወ እና የ በመካከል የሚገኙባቸው ግእዛውያን ቃላት፡- የወ ማስረጃ በቀተለ ቤት ረወሰ ብሎ ይረውስ ይርውስ ይርውስ ዐወረ ብሎ ይዐውር የዕውር ይዕውር ይላል የኼውም ዚልቅ ነው ሲኀረድ ግን ረወሰ ብሎ ይረውስ ይሩስ ይሩስ ዐወረ ብሎ ይዐውር ይዑር ይዑር ይላል፡፡
የየ ማስረጃ በቀተለ ቤት ገየሰ ብሎ ይገይስ ይግይስ ይግይስ ሠየጠ ብሎ ይሠይጥ ይሥይጥ ይሥይጥ ይላል የኼውም ሲዘልቅ ነው ሲኀርድ ግን ገየሰ ብሎ ይገይስ ይጊስ ይጊስ ሠየጠ ብሎ የሠይጥ ይሢጥ ይሢጥ ይላል፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ግሶች ሁሉ ዘንድና ትዕዛዝ አንቀጻቸው ዘልቆም ኀርዶም የነበባል ማለት ነው፡፡

፪. በአ እና በወ የሚነሱ ግሶች ካልአይ፣ ዘንድና ትዕዛዝ አንቀጻቸው መነሻቸውን ኀርደው ይነበባሉ፡፡ ለዚሁም ማስረጃ አድለወ ብሎ ያደሉ ያድሉ ያድሉ አጥረየ ብሎ ያጠሪ ያጥሪ ያጥሪ ወሀበ ብሎ ይሁብ የሀብ የሀብ ሲል ወደየን ወረደን የመሳሰሉት ግሶች ደግሞ ይወዲ ይደይ ይደይ፣ ይወርድ ይረድ ይረድ እያለ ዘንድና ትእዛዙ አንቀጻቸውን ኀርደው ይነበባሉ፡፡

፫. ደጊመ ቃል የሌለው በወ እና በየ የደረሰ ግስ ይኀርዳል እንጅ አይዘልቅም የወ ማስረጃ በቀደሰ ቤት ሐሰወ ብሎ የሔሱ ይሐሱ ይሐሱ ፌነወ ብሎ ይፌኑ ይፈኑ ይፈኑ ይላል፡፡

፬. ደጊመ ቃል ያለው በወ እና በየ የደረሰ ግስ ይዘልቃል እንጅ አይኀርድም የወ ማስረጃ ለወወ ብሎ የለውው ይልውው የልውው፣ ከወወ ብሎ ይከውው ይክውው ይክውው ይላል፡፡ የየ ማስረጃ በቀተለ ቤት ጕየየ ብሎ ይጕይይ ይጕይይ ይጕይይ፣ በባረከ ቤት ጻሕየየ ብሎ ይጻሐይይ ይጻሕይይ ይጻይይ፡፡

### ፰.፰. የሥም አነሳስና አጣጣል ሥርዓተ ንባብ

ይህ የንባብ ዓይነት በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በሚነበቡበት ጊዜ የምንሰማው የንባብ ባሕል ነው፡፡ የኼውም አማኑኤል፣ ሔዋን፣ ኢሳይያስ፣ ጳውሎስ የመሳሰሉ ሥሞች በኃያል ድምጽ አዳም፣ ሙሴ፣ ማርያም፣ ክርስቶስ የመሳሰሉ ሥሞች ደግሞ ዝቅ ባለ በንዑስ ድምጽ ተጥለው ይነበባሉ፡፡ ይህ ሥርዓተ ንባብ እንዲ በዘፈቀደ ወይም በልማድ ሳይሆን የራሱ ሕጎች ወይም ቀመሮች ስላሉት ነው፡፡ ሕጎቹ ወይም ቀመሮቹ እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

**ሀ. የሚነሱ ሥሞች የንባብ ቀመር፡-** እነዚህ ሥሞች የሰው ሥም የቦታ ሥም ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ በኃይለ ቃል ይነበቡ ዘንድ ሊቃውንት በደነገጉት የሥርዓተ ንባብ ቀመር መሠረት የተዋቀሩ ቃላት ወይም ሥሞች ከሆኑ ተነስተው የሚነበቡ ናቸው፡፡ የሚከተሉትን ትንታኔዎች በትኩረት ተመልከት፡፡

፩. ሀ. ሦስት ቀለም ሆኖ በግእዝ ተነስቶ ድርድሩ፡-

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ግእዝ<br>ራብዕ<br>ኃምስ<br>ሳብዕ | | የሆነ ሥም ይነሳል፡፡ ሲነገርም | አረብ<br>አጋግ<br>አዜብ<br>አሞጽ | ያለውን የመሳሰለ ነው፡፡ |

ሰ. በግእዝ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ የሆነ ሥም ይነሳል ሲነገርም፡-

ዘሩባቤል
አማኑኤል ያለውን የመሳሰለ ነው።

፪. በካዕብ ተነስቶ ድርድሩ፡-

ካዕብ
ራብዕ
ኃምስ
የሆነ ሥም ይነሳል። ሲነገርም
ሱቱኤል
ዱማትዮስ
ቡኤዝ
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፫. በሣልስ ተነስቶ ድርድሩ፡-

ራብዕ
ሳብዕ
የሆነ ሥም ይነሳል። ሲነገር ም
ሚሳቅ
ሲሞን
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፬. በራብዕ ተነስቶ ድርድሩ፡-

ካዕብ
ራብዕ
ኃምስ
ሳብዕ
የሆነ ሥም ይነሳል። ሲነገርም
ሣሙኤል
ናባል
ሳቤቅ
ባሶር
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፭. በኃምስ ተነስቶ ድርድሩ፡-

ካዕብ
ራብዕ
ኃምስ
ሳድስ
ሳብዕ
የሆነ ሥም ይነሳል። ሲነገርም
ዜቡል
ኤልያብ
ሴኬም
ኤርምያስ
ቁርሎስ
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፮. በሳድስ ተነስቶ ድርድሩ፡-

ራብዕ
ኃምስ
ሳድስ
ሳበዕ
የሆነ ሥም ይነሳል። ሲነገርም
ብራኤል
ብሔሞት
ብልዮስ
ግዮን
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፯. በሳበዕ ተነስቶ ድርድሩ፡-

ራብዕ
ኃምስ
ሳብዕ
የሆነ ሥም ይነሳል። ሲነገርም
ቶማስ
ሮቤል
ሶፎር
ያለውን የመሳሰለ ነው።

ለ. የማይነሱ ሥሞች የንባብ ቀመር፡- እነዚህ ሥሞች በመጻሕፍት ተጽፈው በሚገኙበት ጊዜ አንባቢ ሁሉ በቀመራቸው መሠረት በተጣይ ንባብ በንዑስ ድምጽ የሚያነባቸው የሥም ዐይነቶች ናቸው። የህም እንደሚከተለው ተተንትኗል።

፩. በግእዝና በራብዕ ተነስቶ የመድረሻው አጠገብ ሣልስ የሆነ ሥም አይነሳም። ሲነገርም፡-

አቡቀለምሲስ
ናብሊስ
ጳኩሚስ
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፪. በካዕብ ተነስቶ ደካማ ቀለም ያለበት ማለት ድኅረ መነሻው ራብዕ ቅድመ መድረሻው ኃምስ መድረሻው ሳድስ የሆነ ሥም ተጣይ ሆኖ ይነበባል። ሲነገርም፡-

ሱራፌል፣ ኡራኤል
ሩፋኤል፣ ሱራኤል
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፫. በሣልስ ተነስቶ ፫ ደካማ ቀለሞች ሲደረድርና ቅድመ መድረሻው፡-

ሣልስ
ኃምስ
ሳብዕ
የሆነ ሥም አይነሳም። ሲነገርም
ጊዮርጊስ
ሚካኤል
ጲላጦስ
ያለውን የመሳሰለ ነው።

፬. በራብዕ ተነስቶ ድኅረ መነሻው ሳድስ ቅድመ መድረሻው ራብዕ መድረሻው ሳድስ የሆነ ሥም አይነሳም። ሲነገርም፡-

ማርያም
ማስያስ } ያለውን የመሳሰለ ነው።

፭. በኃምስ ተነስቶ ድኅረ መነሻው፡-

ራብዕ
ሳድስ } መድረሻው ሳድስ ቅድመ መድረሻው { ኃምስ
ሳብዕ                                                              ሳድስ
                                                                    ሳብዕ } የሆነ ሥም አይነሳም።

ሲነገርም { ፌላሌምሌሞንም
ኤልሳቤጥ
ሄሮድስ } ያለውን የመሳሰለ ነው።

፮. በሳድስ ተነስቶ፡-

ድኅረ መነሻው ሳድስ
ቅድመ መድረሻው ኃምስና ሳብዕ
መድረሻው ሳድስ } የሆነ ሥም አይነሳም። ሲነገርም { እግዚአብሔር
እስጢፋኖስ } ይላል።

፯. ሀ. በሳብዕ ተነስቶ ድርድሩ፡-

ራብዕ
ኃምስ
ሳብዕ } የሆነ ሥም አይነሳም። ሲነገርም { ቶማስ
ሮቤል
ሶፎር } ያለውን የመሳሰለ ነው።

ለ. በሳብዕ ተነስቶ ቅድመ መድረሻው ሣልስ የሆነ ሥም አይነሳም። ሲነገርም፡- ሆለሆርኒስ ይላል።

፰. ፍጹም ሳድስ የሆነ ሥም በተጣይ ንባብ ይነበባሉ እንጅ አይነሱም። ሲነገሩም፡-

እስክንድር
ግብጽ
ቅምር
ሕንድ
ምስር } ያለውን የመሳሰለ ነው።

፱. ባለሁለት ቀለም የሆኑ ሥሞች አይነሱ። ሲነገርም፡- ቡዝ
ካም
ኖህ
አግ
ኖብ } ያለውን የመሳሰለ ነው።

፲. ሀ. የመድሻ ቀለማቸው፡-

ካዕብ
ሣልስ
ራብዕ
ኃምስ
ሳብዕ } የሆኑ ሥሞች አይነሱም። ሲነገሩም { ኢያሱ
ኩሲ
አቢሳ
ሙሴ
ጋይሶ } የሚሉትን የመሳሰሉ ናቸው።

ለ. እነዚህን የመሳሰሉ ሥሞች በሰ ትራስነት ይነሳሉ። ይኼውም ሲታወቅ፡-

በካዕብ፡ ኢያሱሰ
በሣልስ፡ ብንያሚሰ
በራብዕ፡ አቢሳሰ
በኃምስ፡ ሙሴሰ
በሳብዕ፡ ጋይሶሰ } ተብለው ይነገራሉ።

# ዋቢ መጻሕፍት


፩. ዐምደ ግእዝ (መ/ር ዐቢይ ለቤዛ)፤
፪. መጽሐፈ ታሪክ ወግስ (መ/ር አፈወርቅ ተክሌ)፤
፫. መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መርኆ መጻህፍት (ሊቃ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው)፤
፬. ትንሳኤ ግእዝ (መ/ር ደሴ ቀለብ)፤
፭. የካም መታሰቢያ (አስረስ የኔሰው ዘብሔረ ጐጃም)፤
፮. መጽሐፈ ሰዋስው መጽሔተ አእምሮ (ብሔራዊ ቋንቋ ዘኢትዮጰያ - በተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ፲፱፻፹፪ ዓ.ም)፤ እና
፯. ሌሎች፡፡

“ትግሀ ለኧንተ ተዐቢ ፀጋ!!”

ተፈፀመ።